የአሳታሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው

ካለ አሳታሚው ፈቃድ በስተቀር ይህንን መጽሐፍ ማባዛት መቅዳት መተርጎምም ሆነ በማንኛውም ዘዴ ማሰራጨት በሕግ የተከለከለ ነው፡፡

የመጀመሪያ ዕትም የካቲት 2013 ዓ.ም

ቀደምት ስራዎች

ሰባራ ቀለበት 2006 ዓ.ም
ከአጥንት ያልወጡ አጥንቶች 2007 ዓ.ም
ባልደራስ 2009 ዓ.ም
እግዚአብሔር ምን ነካው 2010 ዓ.ም
ሺቦሌት ሲቦሌት የግጥም ሲዲ 2010 ዓ.ም
የማርያም ከበሮ 2011 ዓ.ም

አሳታሚ እና አከፋፋይ
ሄኖክ አሸብር........ (+251-906-11-49-84)

# ምስጋና

በስመ አብ ወስመ ወልድ ወስመ መንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ አሜን፡፡
ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን በመነሣቱ ለሕያው ተስፋና ለማይጠፋ፣
እድፈትም ለሌለበት፣ ለማያልፍም ርስት እንደ ምሕረትህ ብዛት ሁለተኛ
የወለድከኝ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ
አምላክና አባት ተባረክ፡፡

ለአባቴ አሸብር ካሳ
ለእናቴ ጸሀይ አራጌ
ለእህቴ ኢየሩስ አሸብር
ለፓስተር ዳዊት ጥላሁን
ለኤልያብ ጋሻው
ለቄስ ይትባረክ ማሞ
ለጋሻው ዘመነ
ለዘመድ አበበ (አናሞ) ና ሒሩት
ለምህረት በላይነህ እና ለአዱኛ ግርማይ
ለጌድዮን ኪሮስ እና ለሰላም ታምሩ
ለበክብር በላይነህ (ምቾት)
ለልጅአለም ደመቀ
ለየኔነህ ዮሐንስ
ለመኮ ሞባይልና ኤሌክትሮኒክስ (ለደመቀ) ምስጋናዬ
ከልብ ነው፡፡

## ማውጫ

1. የጨዋይቱ ልጅ ነኝ
2. ጥበብ ጠርቶኛል
3. ነኝ አትበል......ነኝ እላለሁ
4. መሞትህን እመን
5. በፍቅሩ ባህር
6. ፍቅር እንደዚህ ነው
7. አያችሁልኝ ወይ?
8. የሞኝነት ጥበብ
9. የእግዚአብሔር ጽድቅ ነኝ
10. የእግዚአብሔር በግ
11. በስላሴ መሀል
12. የእንዴት ፍቅር የለም
13. ኢየሱስ ከሙሴ
14. ህያው ቃል Vs ገዳይ ፊደል
15. የቀራንዮ የፍቅር ጭማቂ
16. ከሳሼ እና ክሱ
17. የኔ ጉዳይ
18. መሸጫ ዋጋዬ
20. የጨዋይቱ ልጆች
21. ፍቅር ብቻ
22. በገዛ ጦራቸው
23. ስቄአለሁ
24. ወልዶ መጣል
25. ምኑን ተገጠመ
26. ልጁን ነው መስማት
27. የቀብሬ ቀን
28. የፍቅር ብቅል
29. ይሄ ነው ገዳይ
31. መሀይም ነሽ ለካ
32. እኔ እንደምወድሽ
33. የእኔና የአንተ ፍቅር
34. ፍቅርህ አይጨምርም
35. ዘሬ
36. መነቀፍ ዕድል ነው
37. የመምሰራች
38. ኀብኘኝ
39. 100% ከኩነኔ ነጻ

40. ላልሞት
41. መጽሐፍ እንደሚል
43. ዕጥፍ ቅባት የለም
46. ልጅነት በዳቦ
47. ጸጋ ክርስቶስ ነው
48. እንኳንም ሳምከኝ
49. አንተ አንተ ነህ
50. ኦ ውዴ
51. ቅኔ........ሳቂ
52. አልተግባብቶ
53. ጋብቻ እና ፍቺ
54. ክርስቶስ ለምን ተነሳ
55. ምርጫ ተሸንፈህ
56. አሜን አትበል
57. የሚለየን ሞት ነው
58. ሕዝበ አሜን ይላል 2
60. በእጅ ብልጫ
61. የዝሞታ ጩኸት
63. እስኪ ልጠይቅህ
64. የወደድከኝ ጊዜ
65. ቴቴሌስታይ
66. የማያልቅ ፍቅር
67. ውዴ እርቃነን ያምራል
70. ከፊደል ያልተገኘ ቃል
71. መካከለኛችን ኢየሱሰ
72. ከሲያል ጽዮን
73. ሰምህ
74. እሠይ እንኳን
75. ምንኛ ታደለች
76. የድንጋይ ላይ ፊደል
77. ሰካራምስ እኔ
78. ጸድቄ........አለሁ
79. የማይጠገብ ስም
81. የበዛ እንጀራና ያበዛ እንጀራ
82. ጩካኝ ፍቅር
83. አዲስ ፍጥረት
84. ሁሉ በእርሱ
85. እንጀራ እና ውሀ
86. ጨለማ እና ብርሀን

77. አንተን የበላ
78. የነፍሴ ሞቶት
79. ኢየሱስን ያየ
80. እንዲህ ነው ነገሩ
81. ከሰንኜ በላይ
82. በእርሱ
83. ኢየሱስ በሚለው
84. በሕይወት ሞት
85. ቀኝ እና ግራ
86. የሰብከት ሞኝነት
87. ባይገርመኝ ይገርማል

# መግቢያ

"በሩ እኔ ነኝ ፤ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል፤ ይገባልም ይወጣልም
መሰማርያም ያገኛል።"
የሐ 10፡9

## የጨዋይቱ ልጅ ነኝ

ባሪያ እናት ልጅ ወልዳ፤ ጨዋ ነህ ብትለው
መቸም ጨዋ አይሆንም፤ ጨዋነት የዘር ነው
ባሪያይቱ ደጋግማ፤ እልፍ ብትወልድም
እልፍ ባሪያ እንጂ፤ አንድ ጨዋ አትወልድም
ባርያ የወለደችው፤ ሲስቅ ደስ የማይላት
ባርነት የማታውቅ፤ እናቴ ጨዋ ናት

ባሪያይቱ ልጇ ጋር፤ ካልወጡ የምትል
እስማኤል በይስሀቅ፤ አይስቅም የምትል
አብሮ ከልጄ ጋር፤ አይወርስም የምትል
የወለደችውን፤ የምታቀማጥል
ልጇን ለነፃነት፤ ወላጅ ናት እናቴ
የተወለድኩበት፤ ዘር ነው ጨዋነቴ

እኔስ የማይጠፋ፤ የማይሞት ዘር አለኝ
የእመቤቲቱ፤ የጨዋይቱ ልጅ ነኝ
አውቃለሁ እናቴን፤ ሞግዚት አያሻኝም
ባሪያይቱን ፍለጋ፤ ሞኝኛ አልሞኝም
ከጽዮን በስተቀር፤ ከሲናይቱ አልሰማም
የሳራን ጡት እንጅ፤ የአጋርን አልጠባም
እምቢየው

``.....ስለዚህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ የጨዋይቱ ልጆች ነን እንጂ የባሪያይቱ አይደለንም።``
—ገላትያ 4: 31

## ጥበብ ጠርቶኛል

ጥበብ ጠርታኝ የሚል ፤ ብዕር የጨበጠ
ከቃላት መካከል ፤ ቃላት የመረጠ
ከአለም ቀድቶ ፤ ስላለም የሚጽፍ
ሺህ ጊዜ ቢጠበብ ፤ እልፍ ጊዜ ቢጽፍ
ክርስቶስ ካልሆነ የጥበብ መልዕክቱ
ሞኝ ነው ተጠሪ ፤ ሞኝ ናት ጠሪይቱ

እና ምን ልልህ ነው

ያለምን ጥበብ ፤ ሳታውቅ እግዚአብሔር ፤ ሞኝ እንዳ'ረጋት
ጥበብ ከሩቁ ፤ ጠራችኝ ብለህ ፤ አቤት አትበላት

ደሞ እንዲህ እላለሁ............
ካለሁበት መ'ቶ ፤ ጥበብ ጠርቶኛል
ከብዕር በፊት ፤ ህይወት ሰ'ቶኛል

**``ለተጠሩት ግን፥ አይሁድ ቢሆኑ የግሪክ ሰዎችም ቢሆኑ፥ የእግዚአብሔር ኃይልና የእግዚአብሔር ጥበብ የሆነው ክርስቶስ ነው።``**

**— 1ኛ ቆሮንቶስ 1 ፥ 24**
**ክርስቶስን የማያሳውቅ ይልቁንም የሚሰውር ጥበብ ሞኝነት ነው!!**
**ሁላችንንም ጥበብ ጠርቶናል!! ክብር ለእግዚአብሔር ጥበብ ለክርስቶስ!!**

## ነኝ አትበል . . . ነኝ እላለሁ

ጻድቅ ነኝ ብል...........ተደርጌ
ቅዱስ ነኝ ብል..........ተደርጌ
ልጁ ነኝ ብል............ተወልጄ
ምርጡ ነኝ ብል.........ተመርጬ
በ'ኔ ስቃይ ፤ በ'ኔ ቦታ
እሱ ወስዶ ፤ የ'ኔን ፈንታ
ያለነውር ፤ አደረገኝ
እንከን አልባ ፤ አደረገኝ
የርስት ወራሽ ፤ አደረገኝ
ያለ ኀጢአት ፤ አደረገኝ
እሱ አድርጎ ፤ ነህ እያለኝ
አይደለሁም ፤ ምን አስባለኝ
ነ..........................................ኝ!!

አኔ እንደውም..........
ሲሆንልኝ ያ'ረገኝን
ነኝ የምል ነኝ ነህ ያለኝን!!
✍ ምንድን ነው የሆነልህ?

## መሞትህን እመን

ዛሬ እግዚአብሔርን ፧ አስደስታለሁ
ትዕዛዙን ሁሉ ፧ እጠብቃለሁ
ብለህ ሳትጨርስ ፧ ገና ሳትፈጽም
ሕጉን ተላልፈህ ፧ እዛው ስትቆዝም
አልረባም እያልክ
አልጠቅምም እያልክ
መልካም በማድረግ ፧ ጻድቅ ልትሆን
ለእግዚአብሔር ደስታ ፧ በራስህ ልትኖር
አላምን አልክ እንጂ ፧ ሞቻለሁ ብለህ
ምን ጥያቄ አለው ፧ እንደገደለህ
ጻድቅ መሆንህ ፧ ገና ያልገባህ
ኀጢአተኝነት ፧ ዛሬም 'ሚሰማህ
ከክርስቶስ ጋር ፧ መገደልህን
የሞቱን ጥምቀት ፧ መጠመቅህን
አላምን ብለህ ፧ እንጂ አንተ ሙት ነህ
በኀጢአት ጉዳይ ፧ ጠያቂ የሌለህ
አንተ እኮ ማለት.............
"በድን የሆነ ፧ ማንን ይክሳል
የሞተ ታድያ ፧ ምኑ ይከሰሳል"
የተባልክ ነህ
ኀጢአት ላያገኝህ ፧ በቀሪ የዕድሜህ ዘመን
በህይወት የለህም ፧ መሞትህን እመን

**መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?**
**"ከእንግዲህስ ወዲያ ለኃጢአት እንዳንገዛ የኃጢአት ሥጋ ይሻር ዘንድ አሮጌው ሰዋችን ከእርሱ ጋር እንደ ተሰቀለ እናውቃለን፤ የሞተስ ከኃጢአቱ ጸድቋልና።"**
**— ሮሜ 6 ፥ 6**
**❤ ሞቻለሁ ስል ጻድቅ ነኝ እያልኩ ነው!! ጻድቅ ነኝ ስል ሞቻለሁ እያልኩ ነው!! መሞቴን ቀላል አምኛለሁ!!**

በሄኖክ አሸብር

የቀራንዮ የፍቅር ጫጣቂ

## በፍቅሩ ባህር

የክርስቶስ ፍቅር ፣ ምን ያህላል ብሎ
ይለኛል ጠያቂ ፣ እኔ እመልሳለሁ
ዌል እንግዲህ ብዬ ፣ ልናገር ጀምሬ
ዝም እላለሁ እንጂ ፣ ደሞ ምን እላለሁ?

ፍቅሩማ ስል ገና ፣ እየከዳኝ አቅም
ጀምሬው ነው እንጂ ፣ ጨርሸው አላውቅም
ደግሞስ መች ያልቅና!!

ስፋት ርዝመቱ ፣ ከፍታ ጥልቀቱ
አዕምሮዬን ቢያልፍም ፣ ከብዶኝ ማብራራቱ
ምችት ብሎኛል ፣ በፍቅሩ ባህር ፣ ሁሌ መዋኘቱ!!

የቀራንዮ የፍቅር ጩኸት

# ፍቅር እንደዚህ ነው

ያለ አንዳች ምክንያት፣ እንዲያው እንደመውደድ
የጠላቶችን ሞት፣ በራስ እንደመፍረድ
በገዛ ፈቃዱ፣ ነፍሱን እንደማኖር
ለኀጢአተኛ ሰው፣ ኀጢአት እንደመሆን
ፍቅር እንደዚህ ነው ❤

በደለኛውን ሰው፣ መልሶ እንደመካስ
የኀጥዑን ቀብር፣ ለራስ እንደመማስ
የኀጢአትን ቁጣ፣ በጽድቅ እንደማብረድ
ለአለም ፋሲካ፣ ልጅን እንደማረድ
ፍቅር እንደዚህ ነው ❤

ሰቅለው ለሚገ'ሉት፣ ወደ እንደመሰቀል
የሞታቸውን ምንጭ፣ ከስሩ እንደመንቀል
በጦር ለሚወጉት፣ ፈቅዶ እንደመወጋት
የወንጀለኛን ክስ፣ በሞቱ እንደመዝጋት
ፍቅር እንደዚህ ነው ❤

ሸፋኝ መጋረጃን፣ ከላይ እንደመቅደድ
ከጽዮን መጥቶ፣ ሲኦል እንደመውረድ
የበደለኞችን፣ ፍርድ እንደመሸከም
ታመው የጠሉትን፣ አፍቅሮ እንደማከም
ፍቅር እንደዚህ ነው⊠
በሰደቡት ጊዜ፣ እንዳለመመለስ
አልቃሻ ገራፊን፣ ካይኑ እንባ እንደማበስ
ደካማውን ገፊ፣ ተገፍቶ እንደማቀፍ
ተቀበዝባዥ ገዳይን፣ ተገርፎ እንደማትረፍ
ፍቅር እንደዚህ ነው ❤

የታማሚ ተፊን፣ ደዌ እንደመቀበል
ተሳዳቢዎችን፣ ተሰድቦ እንደማክበር
ስለበደለኛ፣ በደል እንደመድቀቅ
ከአብ የራቀውን፣ ቀርቦ እንደማስታረቅ
ፍቅር እንደዚህ ነው ❤

በሸላቾቹ ፊት፣ እንደመሰቃየት
አንደበቱን ሳይከፍት፣ ሲያርዱት እንደማየት
ለሞት አሳልፎ፣ ነፍሱን እንደመስጠት
ሲበድሉት ጊዜ፣ ይቅር እንደማለት
ፍቅር እንደዚህ ነው ❤

ሳናውቀው ሳንወደው
እኛ እግዚአብሔርን፣ ወደድንህ ሳንለው
እግዚአብሔር እኛን
ቀድሞ እንደወደደን፣ ፍቅር እንደዚህ ነው ❤

**"ፍቅርም እንደዚህ ነው፤ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደወደደን ስለ ኀጢአታችንም ማስተሰሪያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደ ላከ እንጂ እኛ እግዚአብሔርን እንደወደድነው አይደለም።" —1ኛ የሐንስ 4: 10**

በሄኖክ አሸብር

## አያችሁልኝ ወይ?

ከመክበርም በላይ፣ ክብር ሳለ ራሱ
ወደ ጥልቁ ውርደት፣ እጅግ ወርዳ ነፍሱ
ሰው ለዞፋን ሲሞት፣ ዞፋን ትቶ የሞተ
የራሱን 'ማይፈልግ፣ ራሱን የሰጠ
በሞት የማይለይ፣ ሞቶ የሚያሻግር
እንኩ የሚል ወዳጅ፣ አምጡ 'ማይል ፍቅር
አያችሁልኝ ወይ?

የሰውን ልጅ ወደ፣ ሊሞት የማይሞተው
ለአባቱ ፈቃድ፣ ፈቃዱን በመተው
አምላክ ሆኖ ሳለ፣ ከሰውም ተንቆ
ብቻውን ያለአጋዥ፣ ያለ ረዳት ወድቆ
ኀይሉ እንደገል ደርቆ፣ አጥንቱ እስኪቆጠር
በራስ ቅል ጎልጎታ፣ ቀራንዮ መስቀል
በሚሞትላቸው፣ እየተገረፈ
ፍቅር ተሸንፎ፣ ፍቅር አሸነፈ
ለ'ኔ ተሸነፈ
በ'ኔ ተሸነፈ
ስለኔ አሸነፈ
እኔን አሸነፈ
ሰማችሁልኝ ወይ?

## የምኝነት ጥበብ

እንደ ሁለቱ ሕዝብ
ጥበብን ሳልሻ፣ ምልክት ሳለምን
ሕያው ቃል ሰምቼ
በስብከት ሞኝነት፣ እንዲያድነኝ ሳምን
ሲወጉት ባላይም
ኢየሱስ ሲሰቀል፣ ምን ባልገኝ ባካል
የማዳኑ ስራ
የመስቀሉ ቃል ሞት፣ ወልዶኝ ካይጠፌ ቃል
አይቶ የወደደኝን
ሳላየው ብወደው፣ ባንዳች አትገረም
አምኖ ለሚድን ሰው
ከሞኝነት በላይ፣ ጥልቅ ጥበብ የለም
እንደ ሁለቱ ሕዝብ
ጥበብን ሳልሻ፣ ምልክት ሳለምን
ሕያው ቃል ሰምቼ
በስብከት ሞኝነት፣ እንዲያድነኝ ሳምን
ሲወጉት ባላይም
ኢየሱስ ሲሰቀል፣ ምን ባልገኝ ባካል
የማዳኑ ስራ
የመስቀሉ ቃል ሞት፣ ወልዶኝ ካይጠፌ ቃል
አይቶ የወደደኝን
ሳላየው ብወደው፣ ባንዳች አትገረም
አምኖ ለሚድን ሰው
ከሞኝነት በላይ፣ ጥልቅ ጥበብ የለም

"በእግዚአብሔር ጥበብ ምክንያት ዓለም እግዚአብሔርን በጥበብዋ ስላላወቀች፥ በስብከት ሞኝነት የሚያምኑትን ሊያድን የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ሆኖአልና።"
—1ኛ ቆሮንቶስ 1፡ 21

## የእግዚአብሔር ጽድቅ ነኝ

ክርስቶስ ስለኔ፣ ኀጢአት እንደሆነ
ስነግራቸው ጊዜ፣ እውነት ነው እያሉ
እኔ በክርስቶስ፣ ጽድቅ ነኝ ስል ጊዜ
ድፍረትህን በልክ፣ አድርገው ይላሉ
ግን ባይረዱ ነው!!

መጽሐፉ እንዳለኝ.............

እኔን ሊያድነን ወደ
እኔን ሊያስጥል ፈቅዶ
ክብሩን ሁሉ ጥሎ
የተጠላ ሆኖ
አምላክ ኀጢአት ሆነ፣ ባልኩበት አንደበት
ጻድቅ አ'ረገኝ ልል፣ ምነው የማፍርበት

እንደዚህ አይልም ወይ?

"እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ
ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው::"
—2ኛ ቆሮ 5: 21

## የእግዚአብሔር በግ

እንዲያው ለመወደድ
የሚያስወድድ ነገር፣ ስላልተገኘባት
እንዲያው ስትወደድ
አለም ደነገጠች፣ አለም ግራ ገባት
እንዲያው የወደዳት
የራሱን በግ አርዶ፣ በነፃ ብይ ቢላት
ሰርቼ ካልከፈልኩ
አልበላም ትላለች፣ አለምስ ሞኝ ናት

እኔስ በልቻለሁ!!

## በስላሴ መሀል

በስላሴ ዘንድ ትልቅ ኢየሱስ ነው!!

.
.
.
.
.
.
.

በስላሴ ዘንድ ትልቅ አብ ነው!!

.
.
.

በስላሴ ዘንድ ትልቅ መንፈስ ቅዱስ ነው!!

እናልህ ወዳጄ..........

በስላሴ መሀል፣ በሶስቱም አንድነት
ከፍ የሚል ስብዕና፣ ዝቅ የሚል ማንነት
ጌታና ሹም ሆኖ፣ አንዱ ባንዱ መንገስ
በእነሱ ዘንድ የለም፣ መብለጥና ማነስ

## የእንዴት ፍቅር የለም

እንደወደድኳችሁ፣ ተዋደዱ ያለው
ፍቅር እንዲሁ እንጂ፣ ፍቅር መች እንዴት ነው
ኢየሱስ ሲወደን፣ ምክንያት ቆጥሮ አይደለም
የ'ንዲሁ ነው እንጂ፣ የእንዴት ፍቅር የለም

''በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና::''
—ዮሐንስ 3: 16

''እኔ እንደ ወደድኋችሁ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት::''
—ዮሐንስ 15: 12

እርስ በርሳችን የምንዋደደው እግዚአብሔር እንደ ወደደን ነው!!

ወዳጄ:-
እግዚአብሔር እኛን የወደደን እንዴት ነው?

## ኢየሱስ ከሙሴ

ቀድሞ በጨለማ ፧ ይኖር የነበረ
ምህረት ተደርጎለት ፧ በብርሀን ያለ
ክርስቶስ በሰራው ፧ በ'ምነት የፀደቀ
እንዲሁ በፀጋ ፧ መዳኑን ያወቀ
ኢየሱስን ሊያኖር ፧ መሞቱን ያወጀ
ሀጥያት እንዳይከሰው ፧ በደም የተዋጀ
መልሶ እንደገና ፧ ፅድቅ በራስ ብሎ
የእግዚአብሔርን ፀጋ ፧ ከህጉ ቀላቅሎ
ሀጥያት ላለማድረግ ፧ ህግ እየሰበከ
ፅድቅን አይራብም ፧ ፅድቅ የተደረገ
መንግስትን አይሻም ፧ መንግስት የሆነ እሱ
ከንጉሱ ጋራ እርግጥ ፧ ነው መንገሱ

እና እኔ ምን ልል ነው

ኢየሱስ ከሙሴ ፧ አይቀላቀልም
በፀጋ ነው እንጂ ፧ ሰው በህጉ አይድንም

## ህያው ቃል Vs ገዳይ ፊደል

በፊደል 3000 ሞተ
በመንፈስ 3000 ዳነ
ሁሌም ህግ ሲሰበክ
ሁሌም መጋረጃ አለ
ሁሌ ኢየሱስ ሲሰበክ
ሁልጊዜም ህይወት አለ

እናማ.........

በጎልጎታ የሞተለት
ኢየሱስ ነው ፃድቅ ልኩ
ህያው ቃሉን ስበኩ እንጂ
ገዳይ ፊደል አትስበኩ

## የቀራንዮ የፍቅር ጨማቂ

በደል መተላለፍ ፥ ምሬት የሞላውን
　　የአዳምን ሕይወት ፥ ጥፍጠና ሊሰጠው
መስቀል ላይ አድቅቆ
　　እግዚአብሔር ስለኛ ፥ ኀጢአት የጨመቀው
በዘላለም ጣዕም
　　ሕይወትን የሚሰጥ ፥ የፍቅር ጭማቂ
ኢየሱስ ብቻ ነው
　　አንዴ ተጠጥቶ ፥ ለዘላለም አርኪ

እናማ ምን ልል ነው

ገና ደህ ሳለሁ
እንዲያው ያለገንዘብ ፥ ሳልከፍል ገዝቶ
ዳግመኛ ላልደኸይ
ዳግም በጥም ላልደርቅ ፥ ላይጠማኝ ጠጥቶ
የሚያስለፈልፈኝ
በቀን ቀኑን ሙሉ ፥ ኢየሱስ የምለው
አብ የጨመቀልኝ
በነፃ የሚሸጥ ፥ ውድ የፍቅር ጁስ ነው

የጠጣ ያውቀዋል በነፃ ግዙ ለማለት ነው!!

# ከሳሼ እና ክሱ

እንዴት እንደሚወደኝ ፧ አየሁ የፍቅር ጥጉን
ሀጥያት ያላወቀውን ፧ ለኔ ሀጥያት ማድረጉን
ፅድቄ ነው ስል ኢየሱስ ፧ ሰርቶልኝ ነው ስራዬን
ፀጋው በእምነት አድኖኝ ፧ አውቄያለሁ ዋጋዬን
ውዱ ነኝ ለክርስቶስ ፧ የሚወደኝ ስስቱ
ጥልቅ ፍቅር ከ'ኔ ይዞት ፧ ስለኔ ነው መቀጣቱ
በመስቀል ላይ ተንጠልጥሎ ፧ ስለነፍሴ አልፏል ነፍሱ
ከ'ግሬ በታች ተጥሎልኝ ፧ ከሳሼ ወድቋል እንኳን ክሱ

# የኔ ጉዳይ

መጨነቅህ እረፍት ሆነኝ ፣ በቁስልህ ቁስሌ ሻረ
የእኔን ሞት አንተ ወስደህ ፣ ያንተ ህይወት ለኔ ሆነ
በዝምታህ ሳቂ በዛ ፣ በደምህ ላብ ተረጋጋሁ
በህመምህ ፈውስ አገኘሁ ፣ ሲፃል ወርደህ ሰማይ ገባሁ
ባሪያ ሆነህ ልጅ አ'ረከኝ ፣ አጋዥ አ'ተህ እኔ ታገዝኩ
እርቃንህን ተንጠልጥለህ ፣ ልብሴ ሆነህ አንተን ለበስኩ
እንዳላፍር አፍረህልኝ ፣ ተሰቃይተህ የኔን ስቃይ
ስለራሴ መልስ እንዳልሰጥ ፣ ያንተ ሁኗል የኔ ጉዳይ

እና ምን ለማለት ነው
እኔን በተመለከተ እንኳን ለሰይጣን ለእግዚአብሔር መልስ
የምሰጠው እኔ አይደለሁም!!

## መሸጫ ዋጋዬ

ሀጥያት እንዳይከሰኝ
አፋቸው እንዲያዝ ፡ ከሳሾቼ ሁሉ
ቀድሞ በመፅሐፍ
ስላንተ የተፃፈው ፡ እንዲፈፀም ቃሉ
ስለ በደል ስርየት
የሚሰዋውን በግ ፡ ስምህ ልትከዳ
እኔን የወከልከው
የኃጥአን ቁንጮ ፡ ብሩክ ነህ ይሁዳ
ያኔ አንተ ሸጠኸው
በ30 ዲናር ፡ ባንድ የባርያ ዋጋ
እሱ ባርያ ሆኖ
እኔ ነፃ ወጣሁ ፡ እንዲሁ በፀጋ
ደግሞ
በዕዳ ተይዤ
መክፈሉ ቢያቅተኝ ፡ በእስር ስንገላታ
ያኔ በፋሲካ
ስቀለው ስቀለው ፡ በሚለው ጫጫታ
ኢየሱስ ተይዞ
አንተ ልትለቀቅ ፡ ይፈታ ተብለህ
ስለ'ኔ መፈታት
እኔን የወከልከው ፡ በርባን ሆይ ብፁዕ ነህ
ያኔ አንተ ተፈተህ
ኢየሱስ ሲሰቀል ፡ ሲሞት የመስቀል ሞት

ሙት የነበርኩ እኔ
ህያው ሁኛለሁኝ ፤ ለዘለዓለም ላልሞት
ደግሞ
በሽላቾቹ ፊት
ዝም እንደሚለው በግ ፤ ሳትከፍት አፍህን
ቃላት ሳታወጣ
በደንብ ያስረዳኸኝ ፤ ለ'ኔ መሞትህን
ሲዖል እንዳልገባ
ሁሉን የሆንክልኝ ፤ እስከ ሲዖል ወርደህ
አለም ሳይፈጠር
በፍቅሬ የተያዝክ ፤ ወዳጄ ኢየሱስ ነህ
ያኔ አንተ ዕዳዬን
በእንጨት ተንጠልጥለህ ፤ ጨርሰህ ከፍለኸው
ማንም እንዳይገዛኝ
መገዛ ዋጋዬን ፤ ልኬን ደም አ'ረከው

## የጨዋይቱ ልጆች

ሰዎች በፀጋ እንጂ
ህጉን በመጠበቅ ፤ መዳን ስላልቻሉ
የአብ የፍቅር ጥግ
የመውደዱ ልኬት ፤ ስጋ ሆኗል ቃሉ
ህጉን እየጠበኩ
በፀጋ ድኛለሁ ፤ ማለት ስህተት ነው
በአሮጌ አቁማዳ
አዲስ የወይን ጠጅ ፤ እንደ መጨመር ነው
ህጉ መግደል እንጂ
ሳይሰሩ ደመወዝ ፤ መክፈልን አያውቅም
ፀጋ እየተወራ
ከኢየሱስ ጋር አብሮ ፤ ሙሴ አይሰበክም
ባሪያ ልጅ ቢወልድም
እንደሱ ባሪያ እንጂ ፤ ወራሽ አያደርግም

እናማ ምን ልል ነው

እኛ ባርያ ሳንሆን
ልንወርስ የተወለድን ፤ ልጅ ነን እያላችሁ
የጨዋይቱ ልጆች
የባርነት ሰፈር ፤ ምን ትሰራላችሁ

ማለቴ.................

ባሪያይቱን አጋርን
ልጇ ጋር ማባረር ፤ አብርሃም ባይወድም
እስማኤል እንዲወርስ
ሳራ ትቅርና ፤ እግዚአብሔር አይፈቅድም
ማለቴ ነው!!

# ፍቅር ብቻ

ኀጢአተኛ ናችሁ ብሎ ፡ ያላራቀን በጥላቻ
ለዘላለም አንዴ ሰ'ቶ..........
ፍቅር ብቻ
ሰላም ብቻ
ህይወት ብቻ
ደስታ ብቻ
ፅድቅ ብቻ
ድነት ብቻ
ፀጋ ብቻ
ምህረት ብቻ
በፍቅሩ ያሸነፈ ፡ ሳይሸነፍ ለጥላቻ
የኔ ወዳጅ ፡ ኢየሱስ ብቻ

## በገዛ ጦራቸው

የክበርን ጌታ
አላወቁት ኖሮ ፤ ሲሰቅሉት መስቀል ላይ
ተጋርዶ የነበረው
የጥል መጋረጃ ፤ ተቀደደ ከላይ
ሰቀለው ሰቀለው
ከሚሉት መካከል ፤ አንዱ ሆኘ ብገኝ
ስርየት አግኝቸ
አብ በራሱ ታርቆኝ ፤ ልጁ ልጅ አ'ረገኝ

እንዴት አትሉኝም..........

እንግደለው ብለው ፤ መስቀል አዘጋጅተው
ኢየሱስ እንዲሞት ፤ ሞት ቢደግሱለት
በገዛ ጦራቸው ፤ መልሶ ወግቷቸው
ለራሳቸው ሆነ ፤ ለሱ ያሉት ስቅለት

ሰይጣንን ሊቀጣ ፤ ለኔ ህይወት ሊቸር
እንዲያው አሳልፎ ፤ ነፍሱን ቢሰጣቸው
አገኘነው ሲሉ ፤ በሞቱ ገ'ሏቸው
እሱ ህያው ሆነ ፤ እነሱን ቀብሯቸው

እና እኔ ምን ልል ነው
እኔ ህያው ሆኜ እነሱ የሞቱት እንግደለው ብለው የገደሉት ቀን
ነው!!

## ስቄአለሁ

እፎይ በማይገልፀው
ሰላም እና ደስታ ፤ ፍቅር በሆነ አለም
በ'የሱስ ክብር ልክ
ከኢየሱስ ጋራ ፤ ሊኖር ለዘላለም
ትንሳዔ ትርጉሙ
ድጋሜ አለመሞት ፤ መሆኑ የገባው
ሞቱ የሞተለት
ደስታው ከሳቅ አልፎ ፤ ያግዘዋል እንባው
ባለ እርሻው አግኝቶት
ሁሉን ያወረሰው ፤ አይሻም መቃረም
እግዚአብሔርን ወርሶ
በኢየሱስ የሳቀ ፤ አያለቅስም ባ'ለም

## ወልዶ መጣል

ከምተነፍሰው ከ'ስትንፋሴ
አንተ ትቀርባለህ ኢየሱሴ
የሩቅ አይደለህም በውስጤ ነህ
መኖሪያህ ሁኛለሁ በልቤ አለህ
ወዴት ነው ያለኸው አልልህም
በሩቅ እንዳለ ሰው አልጠራህም
ናልኝ አትሂድብኝ መቼ እላለሁ
በእኔ ታድራለህ ባንተ አድራለሁ
አ'ጥለኝም አተወኝም
ትተዋለህ አላልከኝም
የያዝከው ሰው ካንተ አይወድቅም
ወልዶ መጣል አንተ አታውቅም

- መተው
- መጣል
- መርሳት
- መጥላት ወዘተርፈ ያንተ በሀሪ አይደሉም!!

❤ የወደድከኝ ላትጠላኝ የወለድከኝ ላትጥለኝ ነው!!
ትወደኛለህ ❤ ❤ ❤

# ምኑን ተገጠመ

የዘማሪው መዝሙር ፧ የገጣሚው ግጥም
ሊናገር ካልቻለ ፧ የክርስቶስን ስም
ማዜሙም መግጠሙም ፧ ለጌታ ካልዋለ
ጥበብ ለጠቢቡ ፧ ለኢየሱስ ካልሆነ
ምን ዋጋ አለው ዜማ
ምን ዋጋ አለው ቅኔ
ምን ዋጋ አለው ስንኝ
ምን ዋጋ አለው ቃሌ
ለኢየሱስ ተገጥሞ ፧ ለ'ሱ ካልተዜመ
ምኑን ተገጠመ ፧ ምኑንስ ተዜመ
የቋጠረው ስንኝ ፧ ኢየሱስ ከሌለው
የገጣሚው ግጥም ፧ ንፋስ መከተል ነው
ለኢየሱስ ካልሆነ ፧ ቢሰደር እልፍ ቃል
ግጥም ሁሉ ቤቱን ፧ በከንቱ ይመታል

# ልጁን ነው መስማት

" መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም፤
በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው።"
(የዮሐንስ ወንጌል 1: 18)

እግዚአብሔር ማነው ብለህ ስትጠይቅ
ያላየን ኢዮብ አትጠይቀው፤
ያላየች ሀናን አትጠይቃት፤
በእቅፉ ያለ የተረከውን፤
የተላከውን ልጁን ነው መስማት።

## የቀብሬ ቀን

መኖሪያው ልሆን ፤ በመገደሌ
ለኢየሱስ ሆኗል ፤ መሞት መኖሬ
ለራሴ ላልኖር ፤ ለራሴ ላልሞት
ቀብሬን ፈፀመው ፤ የጌታዬ ሞት
በጥምቀት በኩል ፤ ተባብሬያለሁ
የኢየሱስ ሞት ፤ የቀብሬ ቀን ነው!!

## የፍቅር ብቅል

ልክ ነህ አንተ ፧ ሰክሬያለሁኝ
አልሰከርኩም ብል ፧ እዋሻለሁኝ
ደግመው ደጋግመው ፧ ካልጠጡ በቀር
ከየት ይገኛል ፧ ሳይጠጡ መስከር
መንፈሱን ሞልቶኝ ፧ ሲያሳጣኝ አቅም
ፍቅር ጠጥቼ ፧ እንዴት አልሰክርም
አብ ያለመጠን ፧ እንዲያው አፍስሶት
ሁለንተናዬን ፧ እሱ ቀድሶት
ከልኬ በላይ ፧ ጠጥቼ ፍቅሩን
ወድጄዋለሁ ፧ ሰክሮ መኖሩን
የማያጣላ ፧ አንዱን ካንዱ ጋር
ጌታ ፍቅር ነው ፧ የሚያስብል ስካር
በፍቅር ገመድ ፧ ፍቅር የሚገምድ
ራስ የሚያስት ፧ ገራሚ መውደድ
በልቤ ፈሶ ፧ ውስጤን ሲያጋግል
ለጥሜ እርካታ ፧ ሰ'ቶኝ ግልግል
ከመንፈሱ ውጭ ፧ ጉሽ ሳልቀላቅል
ሰካራም ሆንኩኝ ፧ በፍቅር ብቅል
ልክ ነህ አንተ
ጉሽ የወይን ጠጅ ጠግቤ መስሎህ
        ያሰከረኝን እንጂ የሳትከው
ሰካራም ሆኗል ብለህ ያልከኝ ልጅ
    አልተሳሳትክም ልክ ነው ያልከው!!

## ይሄ ነው ገዳይ

ሰቀልነው ሲሉ ፤ የሰቀላቸው
ቀበርነው ሲሉ ፤ የቀበራቸው
ሰይጣንን ገፎ ፤ እርቃን ያ'ረገ
ያለቀሱትን ፤ ከልብ ያሳቀ
የእባቡን ራስ ፤ የቀጠቀጠ
ለሙታን ሁሉ ፤ ህይወት የሰጠ
ሽታው የፍቅር
ድምፁ የፍቅር
መጠሪያው ፍቅር
ምግባሩ ፍቅር
የጠጡት ጊዜ ፤ ሰው የሚያሰክር
ይሄ ነው ፍቅር

የዕድሜው ዘመን ፤ የማይቆጠር
ፊቱ ሰዎች ላይ ፤ የማይቋጠር
በሞቱ ሞትን ፤ ወግቶ የገደለ
ከዲያብሎስ አፍ ፤ እኔን ያስጣለ
ለሟች ለመሞት ፤ ለነፍሱ ያልሳሳ
ባሪያ ለማድረግ ፤ ጆሮ 'ማይበሳ
ሰይጣን ሲያዘጋጅ ፤ የመስቀልን ሞት
እንደሚነሳ ፤ ተናግሮ 'ሚሞት
ያለምን ብልጠት ፤ በሞኝነቱ
ሞኝነት 'ሚያደርግ ፤ ድል በመንሳቱ

ሲከዱት ጊዜ ፡ በቀል 'ማያስብ
ሄዶ እንደገና ፡ የሚሰበስብ
"ባለፈው እኮ" ፡ ብሎ 'ማይጠቅስ
በቸርነቱ ፡ ሰው የሚመልስ
ይሄ ነው ጀግና

አንድን መስዋዕት ፡ ለዘላለሙ
መንፈስ በሆነ ፡ በህያው ደሙ
ዳግመኛ ላይሞት ፡ አንዴ ያቀረበ
የበዳዮችን ፡ በደል ያጠበ
ሀጥያተኛውን ፡ ፅድቅ ያደረገ
ከአሮን ክህነት ፡ እጅግ የላቀ
ከሙሴ ፊደል ፡ በሚሻል መንፈስ
ሞትን በመሻር ፡ ህይወት የሚያፈስ
ከመላ'ክት ይልቅ ፡ እጅግ የሚበልጥ
ሁሉ ከ'ግሩ ስር ፡ የተገዛለት
ህያው መስዋዕት ፡ ላባቱ ያስገባ
ስለኔ ቀድሞ ፡ ሰማይ የገባ
አሁን በአብ ቀኝ ፡ የተቀመጠ
እኔንም ከሱ ፡ ጋር ያስቀመጠ
ይሄንን ታላቅ ፡ ሊቀ ካህን ነው
አፌን ሞልቶ ፡ አለኝ የምለው
ገ'ሎ ያስወገደ ፡ የሞቴን ጉዳይ
ይሄ ነው ጀግና ፡ ይሄ ነው ገዳይ

## መሀይም ነሽ ለካ

አለም ሆይ ወዴት ነው ፣ መርማሪ ጠቢብሽ
በእግዚአብሔር ሞኝነት ፣ ተሞኝ ጥበብሽ
በጥበብሽ ብዛት ፣ ጌታን ያላወቅሽው
የሌለ ሞኝ ነሽ ፣ ለካ እኔን ሞኝ ያልሽው
የክብርን ጌታ ፣ አውቀሽውስ ቢሆን
አትሰቅይውም ነበር ፣ እንዲህ ጉድ ለመሆን
ቸነከርኩት ስትይ ፣ እየቸነከረሽ
በደገሺለት ሞት ፣ እሱ እየገደለሽ
ገደልኩት የምትይ ፣ መቃብር ሲዘጋ
ትንሳዔ 'ማታውቂ ፣ መሀይም ነሽ ለካ

ደሞ ....... ደሞ
ደቀ መዛሙርቱ ፣ ሰርቀውት ነው ብለሽ
ውሸት ለማስወራት ፣ ገንዘብ እየከፈልሽ
የ'የሱስን ከሞት ፣ መነሳት ስትክጂ
ቀልድሽ ሆድ ያሳ'ማል ፣ አንቺ እኮ አትቀልጂ!!

ኧረ ደሞ ደሞ
መቃብር ጠብቁ ፣ ብለሽም ከፍለሻል
አልተነሳም በሉ ፣ ብለሽም ከፍለሻል
ተሰርቆ ነው በሉ ፣ ብለሽም ከፍለሻል
ለካ የራስሽ ቀልድ ፣ አንቺንም አሞሻል
በይ እግዜር ይማርሽ!!

## እኔ እንደምወድሽ

ይሄውልሽ ውዴ.......
ያን ጊዜ በእንባሽ ፣ እግሬን ባታርሽም
የብልቃጡን ሽቱ ፣ ሰብረሽ ባታፈሽም
ከበውኝ ቁጭ ያሉት ፣ "እሷ'ኮ" ባይሉሽ
በሹክሹክታ ጩኸት ፣ እያለሽ ባያሙሽ
የተማርሽበትን ፣ ፍቅር ባትገልጭም
እግሮቼን በፀጉርሽ ፣ በ'ንባሽ ባታብሽም
አብ እንደሚወደኝ ፣ እኔ እንደምወደው
በዛኑ መጠን ነው ፣ አንቺን የምወደው!!

ሰሚኝማ ውዴ.......
ዘማዊ ናት ብለው ፣ እንውገራት ባይሉሽ
ጻድቃኖች ቢሆኑ ፣ አመንዝራ ያሉሽ
መሬት ላይ በጣቴ ፣ ጎንበስ ብዬ ባልፅፍ
ካንቺ በቀር ሌላ ፣ ሰው ህጉን ባያልፍ
ከከሳሾችሽ ላይ ፣ ክፋትን ባላገኝ
ያለም ሁሉ ሀጥያት ፣ ያንቺ ሆኖ ቢገኝ
እኔ እወድሻለሁ ፣ አብ እንደሚወደኝ!!

እናልሽ ውዴ ሆይ.......
ባል ባልሆኑ ባሎች ፣ ቢቃጠል ዘመንሽ
ገደብን ቢያበጅም ፣ ሳምራዊ መሆንሽ
ውሀ ልትቀጂ ፣ ብትመጪም ባትመጪም
ከ'ኔ ጠጪ ስልሽ ፣ ብ'ጠጪ ባ'ጠጪም
እኔን በልብሽ ውስጥ፣ ብትወጂም ባትወጂም
እኔ እንደምወድሽ ፣ አንቺ አንቺን አትወጂም!!

❤ እኔ እወድሻለሁ ❤ ❤ ❤

በሃኖክ አሸብር

## የእኔና የአንተ ፍቅር

አንተ እኔን ስትወደኝ ፧ ክብርህን በመጣል
እኔ አንተን ስወድህ ፧ ከውርደት ለመዳን
አንተ እኔን ስትወደኝ ፧ ነፍስህን በመስጠት
እኔ አንተን ስወድህ ፧ ነፍሴን ለማስመለጥ
አንተ እኔን ስትወደኝ ፧ እስከነበደሌ
እኔ አንተን ስወድህ ፧ ምክንያቴን ቆጥሬ
አንተ እኔን ስትወደኝ ፧ በሀጥያቴ ሞቴ
እኔ አንተን ስወድህ ፧ ወደኸኝ አይቴ

እናማ ውዴ ሆይ...........

ወደደኝ ብዬ እንጂ
ወደድኩህ በማለት ፧ እኔ አልደነቅም
ሳልወድህ ላ'ጠላኝ ወደኸኛልና
ብጠላህ ነው እንጂ ፧ ብወድህ አይደንቅም!!
❤ ትወደኛለህ ❤ ❤ ❤

## ፍቅርህ አይጨምርም

አሁን በቀደም 'ለት
ስቃጠል ስቃጠል ፤ ነድጄ በፍቅርህ
አሁን በዚህ ሰአት
ውይ የዛሬው ደሞ ፤ ጨመረብኝ ስልህ
የኔ ዕውቀት ነው እንጂ ፤ የመረዳቴ አቅም
አንዴ እየጨመረ
አንዴ እየቀነሰ ፤ ፍቅርህ አይዋዠቅም።
ባለማወቃችን
ፍቅርህ ጨመረብኝ ፤ ብለን ብንልህም
የሚቀንስና
የሚጨምር ፍቅር ፤ ሲጀመር የለህም!!

## ዘሬ

የሆነ ጨለማ ፤ በህይወቴ የለም
የተጠመጠመ ፤ ዘንዶ እኔ ላይ የለም
ተወራርዶ የመጣ ፤ የዘር መርገም የለም
ዘሬ ኢየሱስ እንጂ ፤ ድያብሎስ አይደለም

እናማ ምን ልል ነው

ከሞት አስመልጦ
ስላዳነኝ እንጂ ፤ አዳኜ ነህ ያልኩት
ቢያድነኝም ወይም
ባያድነኝ ብዬ ፤ አይደለም ያመንኩት
ህይወቱን ሰጥቶኝ
መባረክን ባርኮኝ ፤ ገብቼ በሱ አለም
ዛሬ 'ምከተለው
ስላዳነኝ እንጂ ፤ ለመዳን አይደለም
0% ስጋት!!

# መነቀፍ ዕድል ነው

የግብፅን ወይንና ፤ ጨማውን የሚያስንቅ
የፈርዖን የልጅ ፤ ልጅ ከመባል ይልቅ
ስለ ክርስቶስ ስል ፤ ተገፋሁ 'ምትለው
እጅጉን የሚሻል ፤ ባለጠግነት ነው
የታመነ ባሪያ ፤ ልጅ መሆን ያልቻለ
ከነዓን ናት እረፍት ፤ ካልገባሁ ያላለ
ኢየሱስን ከሩቅ ፤ የተሳለመ ሰው
ሙሴ እንደዚህ ካለ ፤ እንዲህ ከገለፀው
አንተማ መቅደሱ ፤ ልጁ ያደረገህ
አድኖኛል እያልክ ፤ ስለሱ ተናግረህ
የተገፋህ ለታ ፤ ልብህ ደስ ይበለው
ኢየሱስን መርጦ ፤ መነቀፍ እድል ነው!!

## የምስራች

በክርስቶስ መስቀል.......
የተሰራልህን ፧ በአለማወቅህ
ዕዳ አለብኝ 'ምትል ፧ ዕዳህ ተከፍሎልህ

እንካ የምስራች..............

ስራና ዳን ከሚል ፧ የኀጢአት ኀይል ሕግ
ከሞት ያመለጥከው ፧ በመዋጮ አይደለም
በሰራሁልህ ኑር ፧ ያለህ ወዳጅ እንጂ
ሰርተህ ክፈል ብሎ ፧ የጠየቀህ የለም!!

ፀጋ ምስክሬ ነው!!

# ጎብኘኝ

ማደሪያህ እንድሆን
በደምህ ቀድሰህ ፤ መቅደስህ አ'ርገኸኝ
በውስጤ እየኖርክ
መኖሪያ ሁንልህ ፤ መኖሪያ ሆነኸኝ
እባክህን አንዴ
እየኝ ተመልከተኝ ፤ ጎብኝኝ አልልህም
በልቤ ኗሪ እንጂ
መ'ተህ የምትሄድ ፤ ቱሪስት አይደለህም!!
ያመንን ሁላችን
የሞተልን ሊኖር ፤ እኛ ተገ'ለናል
እንኪያስ ቤት ከሆንን
መኖሪያ ኗሪውን ፤ እንዴት ጎብኝኝ ይላል?

እረ በፍጡም አይባልም!!

## 100% ከኩነኔ ነፃ

ድነት አገኝ ብዬ ፣ ሳይደክም ጉልበቴ
ሳይታከልበት ፣ የግል ጥረቴ
አንዳች ሳላዋጣ ፣ ለመዳን ሳልሰራ
ሙት በሆንኩኝ ጊዜ ፣ ከክርስቶስ ጋራ
ህይወትን ሰጥቶኝ ፣ ያለ ልክ ከበርኩ
ኢየሱስ ሲሰቀል ፣ ሲሞት እኔም ነበርኩ
ሲነሳም እንደዛው!!

ምን ለማለት ፈልጌ ነው

መ'ቶ እኔን ሊኮንን
ማንም እንዳይደፍር
ኢየሱስ ሰርቶልኝ
ለኔ ተቆጥሮልኝ
ቀይሪያለሁ አለም
የሚከሰኝ የለም!!

-እኔን ሊኮንን የሚሞክር ያፀደቀኝን ማናገር ግድ ይለዋል!!
ኦ.....ለካ እሱንም አይችልም!!

## ላልሞት

እድፈት የሌለበት
ፍፁም ሰው የሆነ ፧ ደግሞ ፍፁም አምላክ
የአባቱን ትዕዛዝ
እሺ ብሎ መጣ ፧ እኔን ሊያድን ሲላክ
በመስቀሉ ስራ
በኢየሱስ መታዘዝ ፧ ህይወትን አገኘሁ
ሙት የነበርኩ እኔ
ላልሞት ከሞት ድኜ ፧ በአብ ቀኝ ተገኘሁ!!

- እንኪያስ ምን እላለሁ? እሠይ!! እፎይ!! እርፍ ነዋ!!

## መጽሐፍ እንደሚል

መጽሐፍ እንደሚል........
ስለኔ የሞተው ፤ ለ'ኔ ሕይወት ሰ'ቷል
የኀጢአት ትብታቤን ፤ እስራን ፈትቷል

መጽሐፍ እንደሚል.......
እግዚአብሔር ሰውን ፤ ከሞት ሊታደገው
ልጁን ኢየሱስን ፤ በደዌ አደቀቀው

መጽሐፍ እንደሚል.........
ስለበደላችን ፤ የእግዚአብሔር በግ ታርዷል
በደሙ ክፍያ ፤ ኀጢአት ተወግዷል

መጽሐፍ እንደሚል.........
የአለምን ሞቶት ፤ በጸጋው ክጃለሁ
ኢየሱስ ሲታረድ ፤ እኔም ታርጃለሁ

መጽሐፍ እንደሚል.........
ሳልሰራ ደመወዝ ፤ ስለሚከፈለኝ
ዳዊት በመዝሙሩ ፤ ብጹዕ ያለኝ ሰው ነኝ

መጽሐፍ እንደሚል........
ወልድ ያለው ሁሉ ፤ አብም ስላለው
አብም ደግሞ አለኝ ፤ በ'ኔ ውስጥ ነው

መጽሐፍ እንደሚል...........
ነህ ያለኝን ሁሉ ፣ ነኝ ብዬ እቆጥራለሁ
እንኳን ነህ እያለኝ ፣ ነህ ያላለኝንም ፣ ነኝ ብዬ ኑሪያለሁ

መጽሐፍ እንደሚል ፣ ብለን ብንናገር
"እኔ እንደመሰለኝ" ፣ ማለት ይቀር ነበር

መጽሐፍ እንደሚል..........
ቅዱሱ መጽሐፍ ፣ ለትምህርት ይጠቅማል
ለተግሣጽ ፣ ይጠቅማል
እንዲሁም ልብንም ፣ ለማቅናት ይሆናል
በጽድቅም ላለ ፣ ምክር ይሆናል
መጽሐፍ እንደሚል ፣ መጽሐፍም ይላል!!

"እኔ ደግሞ የተቀበልሁትን ከሁሉ በፊት አሳልፌ ሰጠኋችሁ እንዲህ ብዬ፦ መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ ኀጢአታችን ሞተ፤ ተቀበረም፤ መጽሐፍም እንደሚል በሦስተኛው ቀን ተነሣ፤"
— 1ኛ ቆሮንቶስ 15 ፥3-4

መጽሐፍ እንደማይል የምንለው መጽሐፍ እንደሚል ስለማንል ነው፡፡ መጽሐፍ እንደሚል እንበል!!

## ዕጥፍ ቅባት የለም

ኑ ትቀባላችሁ
ሰባኪ ነው እንጂ ፧ መጽሐፍ አላለም
አገልጋይ 'ሚቀባው
ሁለትም ሰባትም ፧ ዕጥፍ ቅባት የለም

መጽሐፍ እንደሚል
ቅዱስ የሆነና ፧ በ'ኛ የሚኖረው
የእግዚአብሔር ቅባት
እሺግ ዘይት ሳይሆን ፧ ራሱ ኢየሱስ ነው

እባክህ ጌታ ሆይ
ዕጥፍ ቅባት ቀባኝ ፧ ብለን የምንለው
አንዱ ኢየሱስ ብቻ
አልበቃኝም ብሎ ፧ እንደመሳደብ ነው

ቅባቱ የተሰጠው
ላመነ ሁሉ እንጂ ፧ እየለየ አይደለም
የተካፈለ እንጂ
ከኢየሱስ ውጪ ፧ የተለቀለቀ ፧ የተቀባ የለም

መጽሐፍ ምን ይላል?

"በጌታም የተቀባውን ሳያይ ሞትን እንዳያይ በመንፈስ ቅዱስ ተረድቶ ነበር።"
— ሉቃስ 2 ፥ 26

♥♥♥ ኢየሱስ

"የነቢዩንም የኢሳይያስን መጽሐፍ ሰጡት፤ መጽሐፉንም በተረተረ ጊዜ፥ የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፤ ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና፤ ለታሰሩትም መፈታትን ለዕውሮችም ማየትን እሰብክ ዘንድ፤ የተጠቁትንም ነጻ አወጣ ዘንድ የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እሰብክ ዘንድ ልኮኛል ተብሎ የተጻፈበትን ስፍራ አገኘ።"
— ሉቃስ 4 ፥ 17-19

♥ ♥ ♥ ኢየሱስ

"እናንተስ እኔ ማን እንደ ሆንሁ ትላላችሁ? አላቸው። ጴጥሮስም መልሶ፥ ከእግዚአብሔር የተቀባህ ነህ አለ።"
— ሉቃስ 9 ፥ 20

♥♥♥ ኢየሱስ

"የምድር ነገሥታት ተነሡ አለቆችም በጌታና በተቀባው ላይ አብረው ተከማቹ ብለህ የተናገርህ አምላክ ነህ።"
— ሐዋርያት 4 ፥ 26

♥♥♥ ኢየሱስ

"እግዚአብሔር የናዝሬቱን ኢየሱስን በመንፈስ ቅዱስ በኃይልም ቀባው፥ እርሱም መልካም እያደረገ ለዲያብሎስም የተገዙትን ሁሉ እየፈወሰ ዞረ፥ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበረና፤"
— ሐዋርያት 10 ፥ 38

♥♥♥ ኢየሱስ
"እናንተም ከቅዱሱ ቅባት ተቀብላችኋል፥ ሁሉንም ታውቃላችሁ።"
— 1ኛ ዮሐንስ 2 ፥ 20

♥♥♥ ኢየሱስ
"እናንተስ ከእርሱ የተቀበላችሁት ቅባት በእናንተ ይኖራል፥ ማንም ሊያስተምራችሁ አያስፈልጋችሁም፤ ነገር ግን የእርሱ ቅባት ስለ ሁሉ እንደሚያስተምራችሁ፥ እውነተኛም እንደ ሆነ ውሸትም እንዳልሆነ፥ እናንተንም እንዳስተማራችሁ፥ በእርሱ ኑሩ።"
— 1ኛ ዮሐንስ 2 ፥ 27

♥ ♥ ♥ ኢየሱስ
" ሁላችን በአንዱ በክርስቶስ ተቀብተናል!!አማኝ ሆኖ ያልተቀባ የለም!! Major one ሆኖም special one ሆኖም የተቀባ የለም!!
"በክርስቶስም ከእናንተ ጋር የሚያጸናንና የቀባን እግዚአብሔር ነው፤"
— 2ኛ ቆሮ 1 ፥ 21

የተቀባው ኢየሱስ ነው!! እኛ ደሞ በእርሱ ሁነን የተቀባን ነን!!

## ልጅነት በዳቦ

"እውነት እግዚአብሔር ፤ የ'ርሱ ልጅ ካ'ረገህ
በል እስኪ ድንጋዩን ፤ ብላው ዳቦ አድርገህ"
በሚለው ጥያቄ ፤ ልጅ አይደነግጥም
የሰይጣንን ሀሳብ ፤ ተቀብሎ አይውጥም
ልጅነቱን የሚያውቅ
ሳይበላ አያለቅስም ፤ ሲበላ አይመካም
የልጅ ልጅነቱ
በመወለድ እንጂ ፤ በዳቦ አይለካም!!

እና እኔ ምን ልል ነው?

የእግዚአብሔር ወራሽ ፤ ልጁ ነኝ የምለው
በመብላቴ ሳይሆን ፤ በመወለዴ ነው

ልጅነት በዳቦ አይረጋገጥም!! ልጅነት ያገኘሁት በልቼ ሳይሆን ተወልጄ ነው!!

## ጸጋ ክርስቶስ ነው

"ጸጋ ጸጋ ያልከው
፤ ኃጢአትን ለመስራት ፤ ስለፈለክ ነው"
፤ ብለህ ያልከኝ ጓዴ.
.
.
አንተ አለምን እና ፤ ኃጢአትን የካድከው ፤ በሕግ ነው እንዴ?

እስኪ ይቺን አንብብ

"ይህም ጸጋ፥ ኃጢአተኝነትንና ዓለማዊን ምኞት ክደን፥ የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን፥ ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ እግዚአብሔርንም በመምሰል በአሁኑ ዘመን እንድንኖር ያስተምረናል፤"
— ቲቶ 2 ፡ 12-13

መጽሐፍ ቅዱስ ~ ጸጋ ኃጢአተኝነትን እና አለማዊ ምኞትን ያስክዳል!!

ጓደኛዬ ~ ጸጋ ለኃጢአት ፈቃድ ይሰጣል!!

ኃጢአትን በጸጋ ከካዱ በኋላ ጸጋ ለኃጢአት ፈቃድ ይሰጣል ማለት ኢየሱስ አዳነኝ ካሉ በኋላ ኢየሱስ ገደለኝ እንደማለት ነው!!

## እንኳንም ሳምከኝ

አልፈልግህም ድርሻዬን ስጠኝ ፤ ብየ መጓዜ በራሴ መንገድ
ያሳማ ምግብ እስክመኝ ድረስ ፤ አጉል መውደቄ በምኞት ወጥመድ
በብዙ በደል በብዙ ክፋት፤ የ'ኔ መጨቅየት በኀጢአት ማደፍ
አላገደህም እኔን ከመሳም ፤ አልገደበህም እኔን ከማቀፍ!!

ምን እልሀለሁ?

ባርነት ስመኝ ፤ ልጄ ነህ ያልከኝ
እንኳን አቀፍከኝ ፤ እንኳንም ሳምከኝ!!

❤ ከቆሻሻዬ የጸዳሁት ስታጠብ ሳይሆን ስትስመኝ ነው!!

## አንተ አንተ ነህ

እንደዛ ጊዜ
እንደባለፈው ፤ ልክ እንደ ትናንት
ታጋሽ ይቅር ባይ
መሀሪ እና ቸር ፤ ደራሽ እረዳት
ያይን ማረፍያ
የልብ ድጋፍ ፤ የነፍስ እርካታ
ብርቱ መጠጊያ
ውብ መሸሸጊያ ፤ የውስጥ ደስታ
ስትሰጥ ጊዜ
መንሳት የማታውቅ ፤ መሳይ የሌለህ
ባመታት መሀል
ያው እና ሕያው ፤ አንተ አንተ ነህ
አንዳንዴ መልካም
አንዳንዴ ጨካኝ ፤ ሆነህ አታውቅም
የማሳቅ እንጂ
ሰው የማሳዘን ፤ የለህም አቅም!!

## ኦ ውዴ

ካንተ ገላ ፈሶ ፤ እኔ ላይ ያረፈው
ኀጢአቴን ላይለምደው ፤ በቁጣ የገረፈው
የመዳኔ ፋና ፤ የበደል ስርየቴ
የቸርነት ጅረት ፤ የምሕረት ፏፏቴ
ቁስሌን ፈውሶታል ፤ መቁሰል መታመምህ
ኦ ወዳጄ ስምህ ፤ ኦ ውዴ ያ ደምህ!!

## ቅኔ........ሳቄ

ለሙሾ አጭተውኝ ፧ ቢያፈጡ ቢያፈጡ
ከሳቄ በስተቀር ፧ እንባ ካ'ይኔ ሲያጡ
ምነው ምን አሳቀህ ፧ ብለህ አ'ጠይቀኝ
እንዳለቅስ አይደለም ፧ ኢየሱስ ያሳቀኝ

ታርዶ የሞተልኝ ፧ ስላገኘሁ ምትክ
አልቅስ የሚለኝ ላይ ፧ ከት ብየ ስስቅ
ለጠላቴ ሽብር ፧ ደስታው ደሞ ለኔ
ሁለት ትርጉም አለው ፧ ሳቄም እንደ ቅኔ!!

## አልተግባብቶ

ኢየሱስ ~ እናንተ ምስክሮቼ ናችሁ!!
እኛ ~ አይ እኛ ጠበቆችህ ነን!!

ኢየሱስ እንድንሆንለት የፈለገውን እንጂ እንድንሆንለት የፈለግነውን እንድንሆንለት አይፈልግም!!

ሞት ትንሳዔውን ፧ እንደመመስከር
ስለ ኢየሱስ ፧ በመከራከር
ሸንጥ ገትሮ ፧ ሰርክ መሟገት
ኩበት መልቀም ነው ፧ ላም ባልዋለበት
እማኝነቱን ፧ እንጂ 'ሚያወራው
ጥብቅና አይደለም ፧ ምስክር ስራው!!

✍ ጠበቆች ነን ×
✍ ምስክሮች ነን ✔

## ጋብቻ እና ፍቺ

ኢየሱስ ሆኖ ውድ ባላችን ፤ በጸጋው ከሕግ ተፋትተናል
ላንተሳሰብ 80 ቀደን ፤ ከሞት ጋር በሞት ተለያይተናል
ነፍስ የሚያረካ የሚያረጋጋ ፤ ስሙ ሲጠራ ኢየሱስ ሲባል
ይሄ ነው ወዳጅ ይህ ነው አፍቃሪ ፤ ከሕግ እርግማን የሚቤዥ ባል!!

♥ ኢየሱስ የኛ ቡዔዝ ♥ ♥ ♥

## ክርስቶስ ለምን ተነሳ

እጅጉን ዝቅ ሲል ⁝ እርሱ አንተን ሲሆን
ጽድቁን አጎናጽፎህ ⁝ አንተ እሱን እንድትሆን
እንዳትጠፋ እንጂ ⁝ ፍቅርህ ቢያስገድደው
በኀጢአቱ አይደለም ⁝ በጉ የታረደው

እና እዚህ ላይ ታድያ ⁝ እኔ ምን ልልህ ነው
ክርስቶስ ተነስቷል? ⁝ ስትባል አዎ እያልክ
ጸድቀሀል ስትባል ⁝ አይ ብሎ መመለስ ⁝ ይጋጫል ልልህ ነው
ክርስቶስ ከሙታን ⁝ መነሳቱን አምነህ
እንዴት መጽደቅህን ⁝ ትጠራጠራለህ
ሞት ዳግም ላይገዛው ⁝ ከብሯል ለዘላለም
ተነስቷል እያሉ ⁝ አልጸደኩም የለም!!

"........ስለ በደላችን አልፎ የተሰጠውን እኛን ስለ ማጽደቅም የተነሣውን ጌታችንን ኢየሱስን ከሙታን ባስነሣው ለምናምን ለእኛ ይቈጠርልን ዘንድ አለው።"
— ሮሜ 4 ፥ 24-25

1ኛ ቆሮንቶስ 15

------------

16 ሙታን የማይነሡ ከሆነ ክርስቶስ አልተነሣማ፤
17 ክርስቶስም ካልተነሣ እምነታችሁ ከንቱ ናት፤ እስከ አሁን ድረስ በኃጢአታችሁ አላችሁ።

## ምርጫ ተሸንፈህ

እየዉልህ ሰይጣን...........
ባለጠጋ ዋሾ
ቱጃር ሀብታም ሸንጋይ ፤ እንደሆንክ አልክድም
ቢሆንም ቢሆንም
ይሄንን ሳልነግርህ ፤ ማለፋን አልወድም

ታድያ ምን ልልህ ነው?
ጀግና ነኝ 'ምትለው
አለሁ የምትለው
ያዝኩህ የምትለው

እንደው እኔ 'ምለው............

ሞቴ ተወግዶ ፤ ህይወት የተሰጠኝ
ካንተ ያመለጥኩት ፤ የተሻረው ፍርዴ
በኢየሱስ ክቡር ደም ፤ መንግስትህ ፈርሶ እንጂ
ምርጫ ተሸንፈህ ፤ ይመስልሀል እንዴ?

✍ ሰይጣን ኢዝ Defeated!!

## አሜን አትበል

ራስህን ፈትሽ ~ አሜን አይባልም
እስኪ ራስህን እይ ~ አሜን አይባልም
አንተም አትድንም ፤ መጽሐፉም አይልም!!

እባብ የነደፈህ ፤ ቁስሉ እንዲድንልህ
ወደ ተሰቀለው ፤ የናስ እባብ እንጂ ፤ አትይ ወደ ቁስልህ
የተባለ እስራኤል ፤ ከቁስሉ የዳነው
የተሰቀለውን ፤ ናስ እባብ አይቶ ነው

የአካሉ ጥላ ፤ የኢየሱስ የሆነ
ያ በብሉይ ኪዳን ፤ ምሳሌ ነበረ

ዛሬም እንደዚህ ነው........

ከነደፈህ እባብ ፤ ቶሎ እንድትፈወስ ፤ አዳኝ መ'ቶልሀል
በኃጢአተኛ ስጋ ፤ ምሳሌ ተደርጎ ፤ ተንጠልጥሎልሀል
እያበጠ ካለው ፤ ከቁስልህ ላይ አንሳ ፤ የአይኖችህ ትኩረት
ራስህን ፈትሽ ፤ የሚል ስብከት አምነህ ፤ መሞትን አትምረጥ
ፍርዱን እሱ ወስዶ
አለም ሁሉ እንዲድን ፤ የመጣውን ላለም
የተሰቀለውን ኢየሱስን እንጂ ፤ ቁስሉን ቁስሉን አይቶ ፤ የሚድን ሰው የለም
መጽሐፍ ምን ይላል?
"ሙሴም የናሱን እባብ ሠርቶ በዓላማ ላይ ሰቀለ፤ እባብም የነደፈችው ሰው ሁሉ የናሱን እባብ ባየ ጊዜ ዳነ።" — ዘኍልቁ 21 ፡ 9

## የሚለየን ሞት ነው

የዘች አለም ፍቅር
የመውደድ ጥግ ቃል ፤ የሰርክ ቅኔዋ
"የሚለየን ሞት ነው"
"የሚለየን ሞት ነው" ፤ የሚል ነው ዜማዋ

የኔ ግን ይለያል ፤ የኔ እንዲህ አይደለም
እኔን ከኢየሱስ ፤ የሚለይ ሞት የለም
ጭራሽ ይባስ ብሎ ፤ እንኳንስ ሊለየን
እኔና ኢየሱስን ፤ ሞት ነው ያገናኘን!!

እንዴት አትሉኝም............

እሱ እኔን ፍለጋ ፤ እኔ ከ'ሱ ሽሽት
ሞት በነገሰበት ፤ በውድቅት ምሽት
እንካ ህይወት ብሎ ፤ ፍቅርን ያወጋኝ
በሞቱ እንድደሰት ፤ ሞቶ ነው ያነቃኝ!!

## ሕዝቡ አሜን ይላል #2

የሆነ አገልጋይ
መጽሐፉን ገልጦ ፣ ሕያው ቃል ያወራል
ስለ ድነት መንገድ
ስለ ጸጋው ወንጌል ፣ እንዲህ ይናገራል

እነሆ ደህንነት ፣ መስቀል ላይ ባለቀው
በክርስቶስ ስራ ፣ በጸጋ ብቻ ነው
ሳይጥር እና ሳይግር ፣ ያመነ ይጸድቃል
ስራ ሳያዋጣ ፣ በጸጋ ይድናል
ሕዝቡ አሜን ይላል

ሌላኛው አገልጋይ ፣ በሳምንቱ ይቆማል
ድምጽ ማጉያ ይዞ ፣ ጌታ እንደዚህ ይላል ፣ ማለት ይጀምራል

ስሜ እጅግ ተነቋል ፣ መድረኬ ተደፍሯል
ስለቤቴ ቅናት ፣ ቀስቴ ተገትሯል
ከቁጣዬ መአት ፣ ማንም አያመልጥም
ለጸሎቶቻችሁ ፣ ጆሮዬን አልሰጥም
የመከራ ማዕበል ፣ አውሎ ንፋስ መ'ቷል
ኀጢአተኛ ቀርቶ ፣ ጻድቁም ይሞታል
ማንም ይሄን ወጀብ ፣ መቋቋም አይችልም
አይደለም የበላን ፣ የጾመን አልምርም
እንግዲህ ሕዝቤ ሆይ ፣ አድን ራስህን

በትጋት ፈትሸው ፤ ጓዳና ኪስህን
ማቅ ለብሰን ብናለቅስ ፤ ይራራ ይሆናል
ምናልባት 4 ሰው ፤ ወይ 3 ሰው ይድናል
ሕዝቡ አሜን ይላል!!

ደሞ ሌላ አገልጋይ ፤ በሌላኛው ሳምንት
ምስባኩ ላይ ወ'ቶ ፤ ይናገራል መልዕክት
የተወደዳችሁ ፤ ያባቴ ብሩካን
እግዚአብሔር አባት ፤ ሁሌ እንደዚህ ይላል
ተራሮች ቢፈልሱ ፤ ኮረብታው ቢወገድ
የሰላሜ ኪዳን ፤ የኔ እናንተን መውደድ
ገደብ የለሽ ፍቅሬ ፤ ም'ረት ቸርነቴ
በጎ ስጦታዬ ፤ ጽድቅ በረከቴ
አይርቅም ከ'ናንተ ፤ ቅዱሱ መንፈሴ
ዳግም ላልቆጣ ፤ ምያለሁ በራሴ
ፈጽሞ አልቆጣም ፤ ዳግመኛም አልዘልፍም
ልክ እንደ ኖህ ጊዜ ፤ አጥፊው ውሀ አያልፍም
እናንተን ለማዳን ፤ ልጄን ፊት ነስቸ
ቀራንዮ መስቀል ላይ ፤ ኀጢአትን ቀጥቸ
የ'ናንተ መድኀኒት ፤ የእኔ በግ ታርዷል
ያኔ የ'ኔ ቁጣ ፤ በልጄ ላይ ወርዷል ፤ የዛው ጊዜ በርዷል
የሚያስጨንቃችሁ ፤ ኀጢአት ተወግዷል
ከእንግዲህ አትፍሩ ፤ ወራሾቼ ናችሁ
አፍቃሪ ጠበቃ ፤ ከ'ኔ ዘንድ አላችሁ
አሁን በእኔ ፊት.........

## በእጅ ብልጫ

እግዚአብሔር ሆይ ብለን.............
ስናመሰግነው
ተባረክ ስንለው
ከፍ በል ስንለው
እንዲሆነን እንጂ ፤ ለራሳችን ጥቅም
ምስጋናችን ሄዶ ፤ ዙፋን አይደግፍም
ሰው ጭብጨባ ቸሮት ፤ ዙፋን አልሰጠውም
ሰው ጭብጨባ ነፍጎ ፤ ዙፋን አይነጥቀውም
የኛ እልፍ ዝማሬ ፤ ለሱ ኢምንት አትሞላም
የኛ እልፍ ተቃውሞ ፤ ክንዱን አያላላም
ትናንትናም ዛሬም ፤ ነገም እሱ ያው ነው
ብናመሰግነው ባናመሰግነው ፤ ሁልጊዜም ምስጉን ነው
እልልታ ቆጥቦ ፤ እጁን በማጣጠፍ
የሚሾመው ሆነ ፤ የሚሽረው የለም
ዙፋኑን ራሱ ፤ ዙፋን አ'ርጎት እንጂ
ዙፋን ላይ የወጣው፣ በ'ጅ ብልጫ አይደለም!!

## የዝምታ ጩኸት

እንዲህ አልሀለሁ..........
ውብ ቃላት ካዘሉ ፧ ከበርካታ ድምፆች
ቀልብን ከሚስቡ ፧ ከብዙ ጩኸቶች
ከማራኪ አንደበት ፧ ከእልፎች መካከል
ትኩረቴን ሳላጣ ፧ አይኔ ሳይነቀል
የማይሰብ ነው ባሉህ ፧ ተወስዶ ሀሳቤ
በዝምታህ ጩኸት ፧ ተሰረቀ ልቤ

እንዲህ አልሀለሁ..........

እውነት ለመናገር
ዝም ብለህል እንጂ ፧ ዝም ግን አላልክም
ልቤን ከመወትወት ፧ ላፍታ እንኳ አላረፍክም

ለሰማ ሰው እኮ................

ጩክ እያለ ፧ የሚያወራ
ያዘነ ልብ ፧ የሚጠራ
ይሄ ስቃይ ፧ ያንተ ነበር
ይሄ ፍዳ ፧ ያንተ ነበር
ይሄ ውርደት ፧ ያንተ ነበር
ብሎ የሚል ፧ የሚናገር
ግርፋትህ ፧ ቋንቋ ነበር

ስቅላትህ ፣ ቋንቋ ነበር
መወጋትህ ፣ ቋንቋ ነበር
እኔ ካንተ ወስጀው ነው ፣ ብሎ የሚል የሚናገር
መጠማትህ ፣ ቋንቋ ነበር
የእግርህ መንቃት ፣ ቋንቋ ነበር
የተፋብህ ፣ ቋንቋ ነበር

እንዲህ እልሀለሁ.............

እኔን እንደወደድክ
ፍቅርህን ስትገልጽ ፣ ቃል አልተናገርክም
አፍህን ሳትከፍት
ዝም ብለህ እንኳን ፣ ማውራት አላቆምክም

እናማ ውዴ ሆይ............
አለመናገርህ ፣ ጩሆ በልቤ ላይ
ትኩረቴ አንተ ሆነህ ፣ ካንተ ሌላ እንዳላይ
ደምህን አፍስሰህ ፣ አይኔን እያየኸኝ
ዝም ያልክ ጊዜ ነው ፣ ብዙ ያወራኸኝ!!

አዎ ዝም ብለሀል!! አዎ ዝም አላልክም!!

# እስኪ ልጠይቅህ

አሁን በቀደም ለት ፧ ሞኞች ተሰብስበው
በ'ነሱ ጭብጨባ ፧ እንደቆምክ አስበው
ቢያጨበጭቡልህ ፧ ሞልቶ የሚተርፍህ
ጭብጨባ ቢነፍጉህ ፧ ጎ'ሎብህ የሚያንስህ
እየመሰላቸው ፧ እላፊ ተቁለው
አወቅን ባሉት ልክ ፧ አላዋቂ ሆነው
በማመስገን ፋንታ ፧ ሲያጉረመርሙብህ
ከክብርህ ክብር ላይ ፧ ስንት ቀነሱብህ
እልል አልል ብለው ፧ ስንት አጎደሉብህ

አሁን በቀደም ለት ፧ ጻድቃን ተሰብስበው
ገናናነትህን ፧ ክብርህን አስበው
አዕላፍ ቅዱሳን ፧ ጻድቃን ሲዘምሩ
በክብር ላይ ክብር ፧ ይሁንልህ ሲሉ
ያጨበጨቡልህ ፧ የሰጡህ እልልታ
መስገድ ማምለካቸው ፧ በጠዋታ በማታ
ከዙፋን እንዳትወርድ ፧ ምንኛ ደገፈህ
ምስጋና ሲሰጡህ ፧ ምን ያህል ተረፈህ

ሲሰጡህ ሲነፍጉህ............
ሲሰጡህ ሲነፍጉህ ፧ በዚህ ሁሉ መሀል
ምን ያህል ተርፎሀል ፧ ምን ያህል ጎ'
ሎሀል

በሚል ሁለት ሀሳብ..........
መልሱ እየደነቀኝ ፧ የማይሆን ጥያቄ
እስኪ ልጠይቅህ ፧ የኔ መደነቄ
ሁሉ የሆንክ አንተ ፧ ሁሉ ነገር ያለህ
እንድንሞላልህ ፧ ምን ያህል ጎደለህ፡፡

## የወደድከኝ ጊዜ

ሰማይ የለም ነበር ፡ ገና አልተዘረጋም
ቀን አልተቆጠረም ፡ አልመሸም አልነጋም
ጨረቃ የለችም ፡ በምሽት ላይ ደምቃ
ጸሐይም አታውቅም ፡ ወጥታና ጠልቃ

የወደድከኝ ጊዜ.......
የብሱ ተገላልጦ ፡ ምድር አልተባለም
ውኃ በአንድ ስፍራ ፡ አልተሰበሰበም
ምድር መሽከርከሯን ፡ ገና አልጀመረችም
የሜዳን ቡቃያ ፡ አላበቀለችም

የወደድከኝ ጊዜ.......
ወፎች በሰማይ ላይ ፡ መብረር አልጀመሩም
አራዊቱ ሁሉ ፡ በስም አልተጠሩም
ምድርን ሊያጠጡ ፡ ወንዞች አልፈሰሱም
አሦች በባሕር ውስጥ ፡ አልተንቀሳቀሱም

የመረጥከኝ ጊዜ.......
እኔ እንኳን ራሴ ፡ ገና አልተፈጠርኩም
አንተን አላወ'ኩም ፡ አንተን አልመረጥኩም
ያለነቀፌታ ፡ ያለ እንከን አ'ረከኝ
ህፀፅ የሌለበት ፡ እድፍ አልባ አ'ረከኝ
አለም ሳይፈጠር ፡ ይሄ ሁሉ ሳይሆን
በክርስቶስ መረጥከኝ ፡ በፍቅር እንድሆን

እናማ እንዲህ አልሁህ.......
ሞቴን ልትሞትልኝ ፡ ግድ ያለህ መሞቴ
የዘላለም እረፍት ፡ የሁሌ ሰንበቴ
የሕይወት ቃል ያለህ ፡ ቃል የታጣልህ ቃል
ፍቅር ከሚለው ቃል ፡ ማፍቀርህ ይልቃል ❤ ❤ ❤

## ቴቴሌስታይ (τετέλεσται)

ኤሎሄ ኤሎሄ ፤ ላማ ሰበቅታኒ
ለሚል ታላቅ ጩኸት ፤ እግዚአብሔር ዝም ያለው፤
ለኔ ኀጢአት ዕዳ ፤ የተዘጋ ሂሳብ
ቴቴሌስታይ የሚል ፤ አጥጋቢ መልስ ነው!!

ቴቴሌስታይ!! ተፈጸመ!! ተጠናቀቀ!!

## የማያልቅ ፍቅር

የክርስቶስ ፍቅር ፤ ምን ያህላል ብሎ
ይለኛል ጠያቂ ፤ እኔ እመልሳለሁ
ዌል እንግዲህ ብዬ ፤ ልናገር ጀምሬ
ዝም እላለሁ እንጂ ፤ ደሞ ምን እላለሁ?

ፍቅሩማ ስል ገና ፤ እየከዳኝ አቅም
ጀምሬው ነው እንጂ ፤ ጨርሸው አላውቅም

ደግሞስ መች ያልቅና!! ❤ ❤ ❤

## ውዴ እርቃኑን ያምራል

አብ ፊት ሲያዞርበት ፤ እኔ አፍጥጬ ያየሁት
አይኔን እና ልቤን ፤ መስቀል ላይ የጣልኩት
ሲገረፍ ደስ ያለኝ ፤ ሲሰድቡት የሳ'ኩት
ሲወጉት ከልቤ ፤ ሀሴት ያደረኩት
የ'ሾህ ጉንጉኑን ሳይ ፤ ስቦርቅ የዋልኩት
ሲተፋበት ጊዜ ፤ ታድያለሁ ያልኩት

መች ወድጄ ሆነና..........እነሱ እኮ ናቸው

በሚስማር ፤ ችንክረው
በጦር ፤ ጎኑን ወግተው
በጥፊ ፤ መትተው
እሾሁን ፤ ጎንጉነው
ገላውን ፤ ገርፈውት
ደም በደም ፤ አርገውት

ልብሱን ቀደውበት ፤ ያለ ልብስ ሲገኝ
በፍቅር እያየኝ ፤ ላንተ ስል ነው ሲለኝ
የሱ እርቃን ሲገለጥ
የኔ እርቃን ሲሸፈን ፤ ስለብስ ታወቀኝ
ያኔ የጠላሁት.......
ወጥቶ የመጣው ፤ ከአባቱ እቅፍ
የኔን ሀጥያት ወስዶ ፤ የኔን እድፍ ሲያድፍ

እርቃኑን አይቸው ፣ ፍቅር ይዞኝ እርፍ

ታድያ እኔ ምን ላድርግ.........እነሱ እኮ ናቸው

ፊቱ ላይ ፣ ሲተፉ
ተሳልቀው ፣ ሲፀፉ
እግሮቹ ፣ ሲነቁ
ፊዘኞች ፣ ሲስቁ
ተጠምቶ ፣ ሲጨነቅ
በደሙ ፣ ሲጠመቅ
ኮምጣጤ ፣ ሲያጠጡት
አሳቅለው ፣ ሲሰቅሉት

ልብሱን ቀደውበት ፣ ያለ ልብስ ሲገኝ
በፍቅር እያየኝ ፣ ላንተ ስል ነው ሲለኝ
የሱ እርቃን ሲገለጥ
የኔ እርቃን ሲሸፈን ፣ ስለብስ ታወቀኝ
ያኔ የጠላሁት..........
ወጥቶ የመጣው ፣ ከአባቱ እቅፍ
የኔን ሀጥያት ወስዶ ፣ የኔን እድፍ ሲያደፍ
እርቃኑን አይቸው ፣ ፍቅር ይዞኝ እርፍ

እናማ ምን አልኩኝ..........

ከእልፍ የመረጥኩት ፣ ልብን ይማርካል

ፍቅሩ ያንበረክካል ፤ ይራራል ይምራል
በደም ተለውሶ ፤ ውዴ እርቃኑን ያምራል
የ'ሾህ አክሊል ደፍቶ ፤ ውብ ነው ውዴ እርቃኑን
ስለኔ የወጉትን ፤ እዩትማ ጎኑን
እዩማ ፤ እጆቹን
እዩማ ፤ እግሮቹን
እዩ ቆንዳላውን ፤ አሰውቦታል ደሙ
ፈውሴ ሆኖልኛል ፤ ፍቅር መታመሙ
ዝርግፍ ጌጥ ሳይኖረው ፤ ዝርግፍ ጌጤ ሆነ
ውዴ እርቃኑን ሆኖ ፤ እርቃኔን ሸፈነ

ግን በደንብ ስማኝ........እርቃኑን ነው ስልህ
አንተን ሊያለብስ እንጂ ፤ ልብስ አ'ቶ እንዳይመስልህ
እስከ እግሩ ድረስ ፤ የለበሰ ነው
ወገቡን በወርቅ ፤ የታጠቀ ነው
የራሱ ጠጉር ፤ እጅግ የነጣ
እግሮቹ እንደ ናስ ፤ ግሎ እንደወጣ
ድምፁ እንደ ውሆች ፤ ፊቱ እንደ ፀሐይ
የ'ሳት ነበልባል ፤ አይኖቹን ለሚያይ
ማንም ሰው ቢሆን ፤ በክብሩ ሲያየው
በፊት ለፊቱ መቆም አይችልም
እንደሞተ ሰው ፤ ይወድቃል እንጂ
እንኳን ጠላቱ ወዳጁ አይቆምም

እና ምን ልልህ ነው............

ከእልፍ የመረጥኩት ፤ ልብን ይማርካል
ፍቅሩ ያንበረክካል ፤ ይራራል ይምራል
በደም ተለውሶ ፤ ውዴ እርቃኑን ያምራል
እኛን ጽድቁ ሊያደርግ ፤ ኀጢአት የሆነበት
ይህ ነው ያንተ ያንቺ ፤ ይህ ነው የኔ ውበት

## ከፊደል ያልተገኘ ቃል

ፊደላት ተሳስረው፣ ሆህያት ተጣምረው
የማይመሰርቱህ፣ የምድር መሰረት
ሐረግ የማትሆን፣ ወይ አረፍተ ነገር
የሰው ልጆችና፣ የእግዚአብሔር ሰንበት

እግዚአብሔር የነበርክ፣ ከእግዚአብሔር ዘንዳ
ቃል ሆነህ የወጣህ፣ አለምን ለማጽናት
ያለ መጀመሪያ፣ ያለም መጀመሪያ
ድምድማት የሌለህ፣ የሁሉ ድምድማት

ጸጋን የተሞላህ፣ እውነት የተሞላህ
ብቸኛ መዳኛ፣ እውነት ሕይወት መንገድ
ቤዛ ልትሆነኝ፣ ከፍለህ ልትቤዠኝ
እንደ'ኔ ሰው የሆንክ፣ ከ'ኔ ለመዛመድ
ከዙፋንህ ይልቅ፣ እኔ በልጨብህ
ስጋ ለሆንከው ቃል፣ ባይኖርም ክሽን ቃል
ምንም ባይመጥንህ፣ ምንም ባይገልጽህም
ፊደል እየተፋ፣ ብዕር ላንተ ያልቃል

የሕይወት ቃል ያለህ፣ ሕያው የሆንክን ቃል
ሕያው ያልሆነ ቃል፣ ሊገልጽህ ባይችልም
ቃል ላጣሁልህ ቃል፣ ነፍሴ ትዘላለች
ምላሴም ያወራል፣ ብዕሬም ዝም አይልም

## መካከለኛችን ኢየሱስ

እግዚአብሔር ወደ ሰው
ሰውም ወደ እግዚአብሔር ፤ ማየት እንዲችሉ
ከሰላሴ መሀል
እግዚአብሔርና ሰው ፤ ሆነላቸው ቃሉ

ሰው እግዚአብሔርን ሲፈልግ ፤ እግዚአብሔርም ሰውን
ሲፈልግ የሚያዩት ወደ ኢየሱስ ነው!!

በክርስቶስ ነኝ In Chirist!!

# ከሲኦል ጽዮን

ኀጢአተኛውን፣ ኀጢአት ሲገለው
ኀጢአት ተደርጎ፣ ጽድቅ ሊያደነው
በክርስቶስ ሞት፣ በደል ከበዳይ
መስቀል ላይ ሞቱ፣ ሟችና ገዳይ
አካኪ ዘራፍ፣ ብሎ ሳይፎክር
ቃል ሳይተነፍስ፣ እንኳን ሊሸልል
ነፍሱን ሰ'ቷቸው፣ ፈቅዶ በራሱ
ገዳዮች ሞቱ፣ ሟቾች ተነሱ
አያውቁት ኑሮ፣ ወግተው ሲገሉት
ቀብራቸው ሆነ፣ ቀብሩ ነው ያሉት
ሊቀር መስሏቸው፣ እንደታረደ
ምርኮ ብዝበዛ፣ ሲኦል ወረደ
ሲነሳ ጊዜ፣ አብረን የሞትነ
ከሲኦል ወ'ተን፣ ፅዮን ገባነ
አለነ

በክርስቶስ In Christ

## ስምህ

ደስታ እያዘለላት
ነፍሴ 'ማትሰለቸው ፤ መቸም የማይደክማት
ልክ እንደቀድሙ
አሁን እ'ሱን ሰምታ ፤ ሗላም እ'ሱን መስማት
ልክ እንደባለፈው
ልክ እንደትናንቱ ፤ ሺህ ጊዜ ብናገር
ኢየሱስ የሚለው
ስሙ እንደሁ ጣፋጭ ነው ፤ አይጠገብ ነገር
የምን ማር ወለላ

## እሠይ እንኳን

አፍህን ሳትከፍት፣ ወደሞት ሲነዱህ
ተጨነክ አሉ አሉ፣ ዝም አልክ እያረዱህ
እሠይ እንኳን ዝም አልክ!!

ስትገረፍ ተረፍኩ፣ ተረግመህ ተባረኩ
ኀጢአት ስትሆን ጽድቅ፣ ባሪያ ሆነህ ልጅ ሆንኩ
እንኳንም ባሪያ ሆንክ!!

የኔ ያንተ ሆኖ፣ ያንተ የኔ ሆነ
ተይዘህ ተለቀኩ፣ ቆስለህ ቁስሌ ሻረ
እሠይ እንኳን ቆሰልክ!!

ተገፋተህ ቀረብኩኝ፣ ተጠምተህ ረካሁ
በህመምህ ዳንኩኝ፣ ሞተህ ከሞት ነቃሁ
እሠይ እንኳንም ሞትክ!!

ድል አ'ርገህ ተነስተህ፣ ሞት ላታይ ዘላለም
ከዚህ አለም ላልሆን፣ ወለድከኝ ካንተ አለም
እንኳንም ወለድከኝ!!
ኢየሱስ ከዚህ አለም አይደለም
እኔም ከዚህ አለም አይደለሁም!!

## ምንኛ ታደለች

እረኛ አላት ነፍሴ፣ አግድም አትውልም
በሚያውላት እንጂ፣ የትሟን አትዞርም
ለምለም መስክ እያለ፣ አትግጥም ደረቁን
ደልቷት ያለችበት፣ አትሻም የሩቁን
በረሀ ብቻ ነው፣ ሀገሩ ነደደ
የሚቀመስ ጠፋ፣ ራብ ሞት ወለደ
የሚል ወሬ ሰምታ፣ አይላላም ወገቧ
በምድረበዳው ላይ፣ ለምለም ሳር ነው ምግቧ
በእረፍት ውሀ ዘንድ፣ አላት የሚመራት
የምትበላው እንጂ፣ የለም የሚበላት
የወራት ፍርርቅ፣ ድርቅ አያሰጋትም
ኑሮዋ ምንጩ ነው፣ ጥማት አይገላትም
በሰላም የምትኖር፣ በጥበቃ ቦታ
የነፍሷ እረኛ፣ ሳይለያት ላፍታ
ድምጹን እየሰማች፣ የምትለመልም
ሌላውን ሳትመኝ፣ ሌላውን ሳታልም
እየተዳበሰች፣ በሰፌ መዳፋ
በጉያው አዳሪ፣ የምትኖር በ'ቅፋ
እርግት እርክት ብላ፣ የተደላደለች
ይቺ የኔ ነፍስስ፣ ምንኛ ታደለች!!

## የድንጋይ ላይ ፊደል

የድንጋይ ፊደል፣ ጽላተ ሙሴ
በመላዕክቱ እጅ፣ ሲወርድ ጊዜ
በኩነኔ ስር፣ ረግጦ ገዝቶ
የሰውን ጀሮ፣ በወሰፌ በስቶ
አድርግ አታድርግ፣ ከፍርድ አጀብ ጋ
ሁሉን ከኀጢአት፣ በታች የዘጋ
ሰርቶም ላይጸድቅ፣ ልፋት ስር ጥሎት
ሕይወት የማይሰጥ፣ የሞት ግልጋሎት
የማያነጻ ፣ ያዳምን በደል
ክቡሩ ገዳይ፣ የድንጋይ ፊደል
ሞቱ በስራ፣ የማይመከት
ኮናኝ ፊደል፣ የሲናው ስብከት
የሚፈጽመው፣ ጀግና ቢታጣ
የተሰፋው ጸጋ፣ ሰው ሆኖ መጣ
የምድር በጎች፣ ማንጻት ባይችሉ
የሰውን ኀጢአት፣ መንቀል ከስሩ
ታርዶ የሚያወርድ፣ ታላቅ ምህረት
እግዚአብሔር ሰጠን፣ ከራሱ በረት
እንደ ናሱ እባብ፣ ተንጠለጠለ
ሁሉን ፈጽሞ፣ ተፈጸመ አለ
ለአለም ሁሉ፣ ታረደ በጉ
ፈጻሚ አግኝቶ፣ ተሸኘ ሕጉ
ፊደሉ ትዕዛዝ፣ ሆኖ ሲገ'ለን
ቃል ስጋ ሆኖ፣ በሞት አዳነን
ከሲኦል ወ'ተን፣ ጽዮን ገብተናል
በፊደል ሞተን፣ በቃል ድነናል

✍ ጸጋ ትምህርት ሳይሆን ኢየሱስ የሚባል ሰው ነው!!

## ሰካራምስ እኔ

ከአብ ልብ ወጥቶ፣ የፈሰሰ ፍቅር
በመስቀል ብርሌ፣ ጠጥቼ ስሰክር
ሕይወት እያስወረኝ፣ እያጻፈኝ ቅኔ
ስካር የሚያምርብኝ፣ ሰካራምስ እኔ

## ጸድቄ..............አለሁ

እኔ ውዳቂ ነኝ፣ አልጠቅምም አልረባም
ደፍሬ በፊትህ፣ ልቆም አይገባም
.
.
.
.
.
.
.
.
.
የምል አይደለሁም፣ አለኝ ታላቅ ድፍረት
ኢየሱስን ለብሶ፣ ደሞ የምን ኀፍረት
ምነው አንገት ልድፋ፣ ልሸማቀቅ ምነው
ክርስቶስ ያፈረው፣ ለማን ሆነና ነው
በአብ መታያዬን፣ ለብሸ አዲሱን ሰው
ታዲያ የት ምኑ ላይ፣ አመድ ልነስንሰው
እንዴት ብየ ልዘን፣ ኬት ይምጣ ለቅሶዬ
ጸድቀሀል እያሉኝ፣ ጌታና ጌታዬ

## የማይጠገብ ስም

ከበሀሪው፣ ከጅምሩ
እውነት የእውነት፣ መምህሩ
ያሳየ እንጂ፣ እየኖረ
እልፍ ፊደል፣ ያልሰደረ
ሰው የማይጥል፣ የማይጠላ
ዞር የማይል፣ እንደ ጥላ
የቃል መአት፣ ሳያንጋጋ
ለፍቅር ሲል፣ የተወጋ
ወዳጅ አለኝ!!

ሁልጊዜ አዲስ፣ ምህረቱ
አይቀየር፣ አይዞር ፊቱ
የማይጠብቅ፣ ጦር ሰብቆ
የማይከዳ፣ ቀን ጠብቆ
ነገር አልቆ፣ ሳለ በቋፍ
'ማያጠፋ፣ የሚጤስ ጧፍ
የሚሸከም፣ እስከ ሸበት
መለዋወጥ፣ የሌለበት
ወዳጅ አለኝ!!

የተናቀ፣ የተጣለ
ለፈውሴ ሲል፣ የቆሰለ
ሲጮህ ጊዜ፣ ያልተሰማ

ለ'ርካታዬ፣ የተጠማ
ስድብ ከፌዝ፣ የጠገበ
ለመዳኔ፣ የታመመ
የሞት መውጊያን፣ ያስወገደ
የአብ ቁጣን፣ ያበረደ
እንዲህ ያለ፣ ወዳጅ አለኝ
ና ዳን ብሎ፣ የገደለኝ
የሞተልኝ፣ የሞትኩለት
የዳንኩበት፣ ያለ ጥረት
ጣፋጭ ስሙን፣ የማልጠግበው
ማንነቱ፣ የስሙ ነው
ኢየሱስን እየጠራ
ማን ጠገበ፣ ማን ራበው?

# የበዛ እንጀራና ያበዛ እንጀራ

ከርሀብ ለመዳን
እዚህ እዛ ቃርመህ፣ በጉርሻ አትዘልቅም
አሁን ብትጠግብ
ኋላ ይርብሀል፣ ሆድ በላሁ አያውቅም
የሕይወት እንጀራ
አምስቱን እንጀራ፣ ቢያበዛ አይግረምህ
የበዛውን ሳይሆን
ያበዛውን ብላ፣ ዳግመኛ እንዳይርብህ

ዳግመኛ የማያስርበው በሕይወት እንጀራ የበዛው እንጀራ ሳይሆን እንጀራውን ያበዛው የሕይወት እንጀራ ነው!!

ኢየሱስ

## ጨካኝ♥ፍቅር

ከእቅፉ አውጥቶ
ለታመመች አለም፣ መድሀኒት ሰዶ
ኀጢአተኛውን ሰው
ብላና ዳን የሚል፣ ንጹህ በጉን አርዶ
ብዙ ልጆች ሊወልድ
ውድ አንድያ ልጁን፣ አንጠልጥሎት በእንጨት
ቅንጣት የማይራራ
ጨካኝ አባት አየሁ፣ ፍቅር አዛኝ አንጀት

"ለገዛ ልጁ ያልራራለት ነገር ግን ስለ ሁላችን አሳልፎ የሰጠው ያው ከእርሱ ጋር ደግሞ ሁሉን ነገር እንዲያው እንዴት አይሰጠንም?"
—ሮሜ 8: 32

## አዲስ ፍጥረት

ከደነቆረች ጨኸታም አለም፣ ከምትለፈልፍ ከማትሰማው
ከ'ልፍ ጫጫታ ካዕላፍ ዋይታ፣ ሕይወት የሚሆን ዝምታ ሰማሁ
ዝምታ ጮኸ ጨኸት ዝም አለ፣ ሞጥ የያዘው በግ ላለም ታረደ
የሁሉን ኀጢአት ራሱ ሆኖ፣ በጉ ሲታረድ ሰው ተወለደ

♥ኢየሱስ♥

## ሁሉ በእርሱ

ጆሮ ሰምቶ የማይጠግበው፣ ሁሌ ሰበር ሁሌ ትኩስ
ያዘነን ልብ የቆሰለን፣ የሚጠግን የሚፈውስ
ለባለ ማቅ ለቅሶኛ አለም፣ የምስራች ተበሰረ
እውነተኛውን የአብ መና፣ ስጋ ብሉ ምስር ቀረ
ለታመሙ በሽተኞች፣ አለን ዜና የሚነገር
የሁሉን ሞት አንዱ ሙቶ፣ አንድ ያረገ ሁለት ወገን
ዘሬ ዘርህ እንዳይባል፣ ላለም በደል በተወጋው
የሁሉ አባት ይዞ ገዳይ፣ አዳም ሞተ ከነቋንቋው
እርቅ ከላይ ለሰው ወርዶ፣ መጋረጃው ተቀደደ
የእኔነት የማንነት፣ ጥል መስቀል ላይ ተወገደ
አይሁድ የለ ግሪካዊ፣ በክርስቶስ ሁሉ አንድ ሆነ
ከዚህ በፊት ኖሮ 'ማያውቅ፣ አዲስ ፍጥረት ተፈጠረ
ሁሉ ሕያው እንዲሆኑ፣ ስለሁሉ አንዱ ሲሞት
በእርሱ ውስጥ አድርጓቸው፣ ሕያው ሆነ በሁሉ ሞት
ሁሉ ከ'ርሱ ሁሉ ለርሱ ፣ ሁሉ በ'ርሱ ተፈጸመ
የኔ ማለት ለኔ ማለት ፣ በኔ ማለት አከተመ

- የሚመካ በእግዚአብሔር ብቻ ይመካ!!
- የሚናገር ስለ ኢየሱስ ብቻ ይናገር!!

# እንጀራ እና ውሀ

ወይ እግዚአብሔር ላይሆን ፤ ወይ በልቶ ላይጠግብ
በድያብሎስ ስብከት ፤ "እንደ" ብሎ ሲያስብ
አዳም በበደለ ፤ ቃል እንዲሞት ታዞ
ፍቅር የሕይወት ምንጬ ፤ ከአብ ልብ ፈሶ
ሰው በልቶ እንዲጠግብ ፤ ጠጥቶ እንዳይጠማው
እንጀራ ተራበ ፤ ውሀን ውሀ ጠማው

የሕይወት እንጀራ♥ኢየሱስ♥የሕይወት ውሀ!!

## ጨለማ እና ብርሃን

ልቡ ተከድኖበት ፤ ታውሮ እየኖረ
ጨለማ ተካፍሎ ፤ በጨለማ ሳለ
በብርሃን ሲያምን ፤ ብርሃን ሆኖ ራሱ
በራሱ ያልበራ ፤ አይጠፋም በራሱ
"ቀድሞ ጨለማ ነበራችሁና፥ አሁን ግን በጌታ ብርሃን ናችሁ፤"
—ኤፌሶን 5: 8

ብርሃንም ጨለማም ዘር ነው!!

## አንተን የበላ

የአባት መና ፤ ሕያው እንጀራ
ዳግም ላታስርብ ፤ የምትበላ
የሕይወት መጠጥ ፤ የዘልአለም
አንተን ጠጥቶ ፤ መጠማት የለም
ሁሉ አንተ ነህ ፤ በሁሉም አንተ
ስለምትክለት ፤ ላንተ የሞተ
ሳይጥር ሳይለፋ ፤ ላቡን ሳይዘራ
እንዴት ይራበው ፤ አንተን በላና
የ ስጋ እንጀራህ ፤ የተቆረሰው
ለኔ ነው ብሎ ፤ ያመነበህ ሰው
ልሙት ቢል እንኳን ፤ አይሆንለትም
አንተን የበላ ፤ ሞት የለበትም

## የነፍሴ ምኞት

ሕይወት ሕይወቴ ነው ፧ መንገድ አድራሻዬ
ጥሜን ቆራጩ አለት ፧ ሕያው እንጀራዬ
ኢየሱስ እያልኩኝ ፧ ብገጥም ባዜመው
አልረካ አልጠማ ፧ አልራብ አልጠግበው
አይለቀኝ አይርቀኝ ፧ አይጥል አይተወኝም
ከ'ርሱ ውጭ ልሻ ፧ ልመኝ አልመኝም

♥ ኢየሱስ ♥

## ኢየሱስን ያየ

አዳምን ያየ ፣ አብን አላየም
ኢዮብን ያየ ፣ አብን አላየም
ዳዊትን ያየ ፣ አብን አላየም
ሙሴንም ያየ ፣ አብን አላየም
አየሁት ቢልም ፣ አይኑ አላየውም
አወ'ኩት ቢልም ፣ አላወቀውም
.
.
.
ኤልያስ እሳት ፣ ማውረዱን ያየ
እግዚአብሔርን ፣ ፈጽሞ አይለይም
ከ'ቅፉ ወ'ቶ ፣ የተረከውን
ወልድን ያላየ ፣ አብን አያይም

ኢየሱስን እይ!!

## እንዲህ ነው ነገሩ

እነርሱ ይቺን ሴት ፡ እንውገራት? ሲሉ
ኢየሱስ አንቺ ሴት ፡ ሰዎቹ የት አሉ?
እኔ ዘንድ ያመጡሽ ፡ ከሳሾችሽ ሁሉ
ብሎ ይጠይቃል
እንዲህ ነው ነገሩ
በሰፈሩት ቁና ፡ ልክ ሲሰፈሩ
እነርሱ መውገሪያ ፡ ድንጋይ እንዲያኖሩ
ሕጉ የተሰጠው ፡ ሙሴ ባይለቅሽም
ጸጋና እውነት የሆንኩ ፡ እኔ አልፈርድብሽም
ብሎ ያጽናናታል
እንግዲህ እንዲህ ነው
በጸጋ ፊት ሕጉ ፡ አቅም ስለሌለው
ኃጢአትን አትስሪ ፡ ፍርዴ ምህረት ነው
እያለ ይላታል
ሕጉ ሞት ፈርዶባት ፡ ጸጋ ይምራታል

# ከስንኜ በላይ

ግጥሜ አንተን ላይገልጽ ፡ ቃላት አቅም ካጡ
ስንኞች ተቋጥረው ፡ ምስልህን ካልሰጡ
አንተን ካላብራሩ ፡ ልክህ ካልሆኑልህ
ካልገለጽኩህማ ፡ ምኑን ገጠምኩልህ
በቃ አልገጥምልህም
ቃላትን እያጣሁ ፡ ቃላት ተጠቅሜ
ጽፌልህ ሳበቃ ፡ ባለኝ በሁሉ አቅሜ
እቅጩን ልናገር ፡ እንደዚህ ነህ ልልህ
ቃል ካጣሁኝማ ፡ ምኑን ገጠምኩልህ
በቃ አልገጥምልህም
በረቀቀ ቅኔ ፡ በሰምና በወርቅ
በስድር ፊደላት ፡ ባልችል አንተን ማወቅ
ገልጦህ የሚጨርስ ፡ ቃል ስላጣሁልህ
በቃ አልገጥምልህም ፡ ብየ ገጠምኩልህ
ብየ ስልህ እኔ
ይህም በመሆኑ ፡ ብዙ ነው እንኳኔ
እንኳን
እንኳን
እንኳን
እንኳን አልተብራራህ ፡ እንኳን በራህልኝ
እንኳን ከአዕምሮዬ ፡ ያለፍክ ሆንክልኝ
እንኳን በግጥሞቼ ፡ ገልጬ አልጨረስኩህ
እንኳን ያላወቅኩህ ፡ እንኳንም አወቅኩህ
እንኳንም ያወቅኩህ ፡ እንኳን አላወቅኩህ
እንኳን ግን አወቅከኝ!!
ከቃል ተወልጄ ፡ ቃል ባጣስ ምናለ
እንኳን የኔ ግጥም ፡ ሊገልጥህ አልቻለ
ከአዕምሮዬ ወ'ቶ ፡ እየተሰነነ
ከአዕምሮዬ በላይ ፡ ይሰኛል ስንኜ
ከስንኜ በላይ!!

ኢየሱስ

## በእርሱ

እግዚአብሔር ሰውን
ሲወድ ያለሰበብ ፤ ችሮት እንድያውን
መውደዱን ሊያስረዳ
የእቅፉን ሲሰጥ ፤ ሳይሸሽግ ጉያውን
በጠለቀ ፍቅር
በወዳጅ እንጀት ልብ ፤ በበዛ ራሮቱ
አመጸኛው ሁላ
አምኖ ይድን ገባ ፤ ከገዳይ ኀጢአቱ
በተትረፈረፈ
በሞት በማይከስም ፤ ሞት አክሳሚ ሕይወት
አለመቻል ብቻ ፤ ይችል የነበረ
ኀጢአተኛው መጽደቅ ፤ ቻለ በ'ርሱ ችሎት
በክርስቶስ!!

## ኢየሱስ በሚለው

በበዳይ አባት ፡ በዳይ በመሆን
እንደሞትኩ እንኳን ፡ ሳላውቅ የምኖር
ሙት ሳለሁ ገና ፡ በአመጻዬ
አጉብጦኝ ሳለ ፡ መአት እዳዬ
ካንተው በሆነ ፡ የፍቅር ግዳጅ
ነፍሴን ታደካት ፡ የኔ እንዲያው ወዳጅ
ፍቅርህ ሲያድነኝ ፡ ከጥፋት አለም
ግድ አለህ እንጂ ፡ ግድ ያለህ የለም
ዳግም ላልጠፋ ፡ ዳግም ላልባክን
አዳኜ ብየ ፡ ስምህን ሳምን
አንዳች ሳልከፍል ፡ ከኔ ኮረጆ
አድነኸኛል ፡ ያለመዋጮ
ፍቅርህ ገብቶኝ ፡ ተረድቶት ልቤ
ስብ ሳይሆን ስምህ ፡ ሆኖኝ ጥጋቤ
አመልክሀለሁ ፡ ማንም ሳያዘኝ
የደስታዬ እንባ ፡ እያገዘኝ

## በሕይወት ሞት

ሰውን ሊያድን ፤ ፍቅሩን ሊያሳይ
ሕይወት ሞተ ፤ መስቀሉ ላይ
ፍቅሩ አግኝቶን ፤ ላንሞት ዳንን
በሕይወት ሞት ፤ ሕያው ሆንን

## ቀኝ እና ግራ

ከአብ እቅፍ ወ'ቶ ፤ አቅፎ ስላስገባኝ
በቀኙ ሁኜ ነው ፤ ግራ የማይገባኝ

## የስብከት ሞኝነት

አይቶ የወደደኝን
ሳላየው ብወደው ፤ ባንዳች አትገረም
አምኖ ለሚድን ሰው
ከሞኝነት በላይ ፤ ጥልቅ ጥበብ የለም

# ባይገርመኝ ይገርማል

ሳልሰራ በስራው ፤ ሳልጥር በልፋቱ
ኢየሱስ በሞተው ፤ በምህረት ሞቱ
ከሞት ተቀስቅሸ ፤ ሕይወት እንካ ስባል
መገረም ቢሳነኝ ፤ ባይገርመኝ ይገርማል




# የሙዚቃ መሳሪያ
# ሞባይልና ኤሌክትሮኒክስ






አድራሻ፦ ሐዋሳ ፒያሳ ሲቲ ሴንተር
አ.አ አማጋ ሕንጻ 45 ሀ
ስ.ቁ 0911340300/0964035983
0916822975